## “በሕግ ፡ ሳይታወቁ ፡ የሚሠሩ” (“ዲ ፡ ፍክቶ”) ፡ እና ፡ ልማዳዊ ፡ የሽርክና ፡ ማኅበሮች ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ።

### ከፖል ፡ ማካርቲ ።

የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ ለመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ በ፲፱፻፶፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡ አብዛኛው ፡ ክፍሉ ፡ በአውሮፓውያን ፡ ሕግ ፡ ላይ ፡ የተመሠረተውን ፡ አንድ ፡ ሰፋ ፡ ያለ ፡ የንግድ ፡ ሕግ ፡ አዘጋጅቶ ፡ አወጣ ። ይህ ፡ የንግድ ፡ ሕግ ፡ አያሌ ፡ አዳዲስ ፡ ፅንሰ ፡ አሳቦችን ፡ የያዘ ፡ ሲሆን ፡ በፊት ፡ ከነበሩት ፡ ፅንሰ ፡ አሳቦች ፡ ውስጥም ፡ አብዛኞቹን ፡ አሻሽሎአል ። የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ፅንሰ ፡ አሳብ ፡ ከነዚህ ፡ ከተሻሻሉት ፡ ፅንሰ ፡ አሳቦች ፡ አንዱ ፡ ነው ። ሁለት ፡ ወይም ፡ ከሁለት ፡ በላይ ፡ የሆኑ ፡ ሰዎች ፡ በአንድነት ፡ የንግድ ፡ ሥራ ፡ የሚያካሂዱባቸው ፡ ድርጅቶች ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ጥቅም ፡ ላይ ፡ ከዋሉ ፡ አያሌ ፡ ዘመናት ፡ አልፈዋል ። የእነዚህ ፡ “የሽርክና ፡ ማኅበሮች” ፡ አቋሞች ፡ እና ፡ የሚመለከቱአቸው ፡ የየቀበሌው ፡ ደንቦች ፡ በጣም ፡ የተለያዩ፡ ሊሆኑ ፡ ይችላሉ ። ከ፲፱፻፶፪ ፡ ዓ ፡ ም፡ በፊት ፡ እነዚህን ፡ ድርጅቶች ፡ በአንድ ፡ ዓይነት ፡ ሕግ ፡ ሥር ፡ ለማጠቃለል ፡ የተደረገው ፡ ማንኛውም ፡ ሙከራ ፡ አጥጋቢ ፡ ውጤት ፡ ሳያገኝ ፡ ቀርቶአል ። እንደ ፡ አስራ ፡ አምስተኛው ፡ መቶ ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ ራቅ ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፡ በፍትሐ ፡ ነገሥት ፡[1] ውስጥ ፡ አንድ ፡ ሙሉ ፡ ምዕራፍ ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ደንቦች ፡ ተጽፈዋል ። በቢዛንታየን ፡ የሕግ ፡ ፅንሰ ፡ አሳቦች ፡ ላይ ፡ የተመሠረተው ፡ ፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥቱ ፡ መደበኛ ፡ (“ኦፊሴላዊ”) ሕግ ፡ ነበር ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ሕግ ፡ ከመንግሥቱ ፡ መናገሻ ፡ ከተማ ፡ ራቅ ፡ ባሉት ፡ ቦታዎች ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ መዋሉ ፡ ያጠራጥራል ። የንግድ ፡ ማኅበሮች ፡ ሕግ ፡ ለንግድ ፡ ድርጅቶች፡ ለሽርክና ፡ ማኅበሮችም ፡ ጭምር ፡ ዘመናዊ ፡ ሕግ ፡ ለማውጣት ፡ የተደረገውን፡ ሙከራ ፡ የሚያሳይ ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ በኢጣሊያን ፡ ወረራ ፡ ምክንያት ፡ የአገር ፡ ውስጥ ፡ የንግድ ፡ ሥራ ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ እንዲካሄድ ፡ የተደረገው ፡ ሙከራ ፡ ኢምንት ፡ ነበር ።

በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ እነዚህ ፡ የንግድ ፡ ድርጅቶች ፡ ሕጉን ፡ የማይከተሉበት ፡ ሕጉም ፡ እነርሱን ፡ የማይመለከትበት ፡ ምክንያት ፡ የለም ። በአንድ ፡ ሕግ ፡ (የንግድም ፡ ሆነ ሌላ) ፅንሰ ፡ አሳብ ፡ መሠረት ፡ ሕጉ ፡ በመስኩ፡ውስጥ ፡ የሚገኙትን፡ጉዳዮች፡ሁሉ፡ማጠቃለል ፡ አለበት ። ስለዚህ ፡ ፓርላሜንቱ ፡ የንግድ ፡ ሕጉን ፡ ሲያጸድቀው ፡ ሊደርስበት፡ የአሰበው ፡ ግብ ፡ ይህ ፡ ነበር ፡ ለማለት ፡ እንችላለን ። ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ በንግድ ፡ ሕጉ ፡ መቅድም ፡ ውስጥ ፡ ሕጉ ፡ “የንግድን ፡ ድርጅቶች ፡ አቋምና ፡ ተግባር ፡ የሚደነግግ ---” ነው ፡ ብለዋል ። ይህ ፡ ሕግ ፡ ከመጽናቱ ፡ በፊት ፡ የተፈጠሩት ፡ የንግድ ፡ ድርጅቶች ፡ ሁሉ ፡ ሕጉ ፡ ከጸናበት ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ በስድስት ፡ ወራት ፡ ውስጥ ፡ ሕጉ ፡ የሚያዘውን ፡ ሁሉ ፡ መፈጸም ፡ ነበረባቸው ። የንግድ ፡ ሕጉ ፡ መኖር ፡ ሳይታወቅ ፡ የተፈጠሩ ፡ የንግድ ፡ ግንኙነቶች ፡ የአሁኑ ፡ ሕጋዊ

1. ፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ ምዕራፍ ፡ ፴፬ ።

ነታቸው ፡ እንዲረጋገጥ ፡ ከንግድ ፡ ሕጉ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ጋራ ፡ መስማማት ፡ አለባቸው፤ በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ በልማዳዊ ፡ ደንቦች ፡ አይሠሩም ። በሌላ ፡ በኩል ፡ ሲታይ ፡ ልማዳዊ ፡ ድርጅቶች ፡ አሁንም ፡ አሉ ። ስለዚህ ፡ ዋናው ፡ ፕሮብሌም ፡ እነ ዚህን ፡ ድርጅቶች ፡ የሚያጠቃልሉና ፡ ከንግድ ፡ ሕጉ ፡ ጋራ ፡ የሚስማሙ ፡ ድንጋጌ ዎችን ፡ ማግኘቱ ፡ ነው ።

የንግድ ፡ ሕጉን ፡ ድንጋጌዎች ፡ ለመፈጸም ፡ አስበው ፡ "የሽርክና ፡ ማኅበሮችን ፡" ካቋቋሙ ፡ በኋላ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ምክንያቶች ፡ የተባሉትን ፡ ድንጋጌዎች ፡ የማይፈጽሙ ሰዎች ፡ ይገኛሉ ። እነዚህ ፡ ሰዎች ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ የውሉን ፡ በጽሑፍ ፡ መሆን ፡ ምዝገባንና ፡ በማስታወቂያ ፡ መግለጽን ፡ የሚመለከቱትን ፡ አስፈላጊ ፡ የመቋቋሚያ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ሳይፈጽሙ ፡ ይቀራሉ ። እነዚህን ፡ ድንጋጌዎች ፡ አለመፈጸም ፡ የሚያ ስከትለው ፡ ውጤት ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ ይተነተናል ። ለጊዜው ፡ ተዋዋዮቹ ፡ በንግድ ፡ ሕጉ ፡ ውስጥ ፡ የተገለጸው ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ የሽርክና ፡ ማህበር ፡ እንዲቋቋም ፡ ስለፈ ቀዱ ፡ ማህበሩ ፡ እንደ ፡ አንድ ፡ የሽርክና ፡ ማህበር ፡ መታየት ፡ አለበት ፡ ለማለት ፡እን ችላለን ። አንድ ፡ ዓይነት ፡ ልማዳዊ ፡ ድርጅትን ፡ በአእምሮአቸው ፡ ውስጥ ፡ በቀረጹት፡ በሁለት ፡ (ወይም ፡ ከሁለት፡በላይ፡በሆኑ፡) ሰዎች ፡ መካከል፡የሚደረገውን ፡ አንድ ፡ ዓይ ነት ፡ ውል ፡ በምንመለከትበት ፡ ጊዜ ፡ ሁኔታው ፡ ትንሽ ፡ ለየት ፡ ያለ ፡ ይሆናል ። እዚ ህ ፡ ላይ ፡ በሰዎቹ ፡ አእምሮ ፡ የተቀረጸውን ፡ ድርጅት ፡ በንግድ ፡ ሕጉ ፡ መሠረት ፡ እንደ ፡ አንድ ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ለመቍጠር ፡ ይቻላል ፡ ወይስ ፡ አይቻልም ፡ የሚ ለውን ፡ "አግባብ ፡ ያለው" ጥያቄ ፡ መጠየቅ ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ። ድርጅቱ ፡ የሽርክና ፡ ማሕበሮችን ፡ በሚመለከቱት ፡ የንግድ ፡ ሕግ ፡ ድንጋጌዎች ፡ መሠረት ፡ ከተቋቋመ ፡ ልክ ፡ ሁለት ፡ ሰዎች ፡ የንግድ ፡ ሕጉ ፡ ተፈጻሚ ፡ እንዲሆንበት ፡ ፈቅደው ፡ እንዳቋቋ ሙት ፡ እንደ ፡ አንድ ፡ የሽርክና ፡ ማህበር ፡ መተዳደር ፡ አለበት ። የዚህ ፡ ዓይነቱ ፡ አባባል ፡ የሽርክና ፡ ማኅበሮችን ፡ የሚመስሉትን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ድርጅቶችን ፡ ይመለ ከታል ፡ ወይ ?

## አሁን ፡ በኢትዮጵያ ፡ ያለው ፡ ሁኔታ ።

በኢትዮጵያውያን ፡ መካከል ፡ ስለሚፈጸሙት ፡ የንግድ ፡ ግንኙነቶች ፡ የተደረገው ጥናት ፡ በጣም ፡ አነስተኛ ፡ ነው ። የዚህ ፡ አንቀጽ ፡ጸሐፊ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ በሚገኙት ፡ ጉራጌ ፡ ነጋዴዎች ፡ መካከል ፡ ስለሚገኙት ፡ የንግድ ፡ ግንኙነቶች ፡ ቅንጅት ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ ጥናት ፡ አድርጎአል ። ቢሆንም ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኘው ፡ ይህ ፡ የጉራጌ ፡ የንግድ ፡ ድርጅት ፡ ብቻ ፡ አይደለም ። የጉራጌው ፡ የንግድ ፡ ድርጅት ፡ የተ መረጠበት ፡ ምክንያት ፡ ብዙ ፡ ነው ፡— ከላይ ፡ እንደተጠቀሰው ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የንግድ ፡ ሁኔታ ፡ የተደረገ ፡ ጥናት ፡ በጣም ፡ አነስተኛ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ማንኛውም ፡ መረጃ ፡ ሊገኝ ፡ የሚችለው ፡ ከነጋዴዎች ፡ ጋር ፡ በሚደረገው ፡ ውይይት ፡ ነው ። በተ ጨማሪ ፡ የሽርክና ፡ ማሕበሮች ፡ በሌሎች ፡ ኢትዮጵያውያንና ፡ በዐረቦች ፡ በሕንዶ ችም ፡ ዘንድ ፡ የሚገኙ ፡ ቢሆኑም ፤ በጉራጌዎች ፡ መካከል ፡ በብዛት ፡ የሚሠራባቸው ፡ የንግድ ፡ ድርጅቶች ፡ ናቸው ። በመጨረሻም ፡ ጉራጌዎች ፡ ቁጥራቸው ፡ አነስተኛም ፡ ቢሆን ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ከሚካሄደው ፡ ንግድ ፡ ከፍተኛውን ፡ ክፍል ፡ ይዘው ፡ ይገኛሉ ። የሆነ ፡ ሆኖ ፡ በዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ የምንነጋገርባቸውን ፡ ሕጋዊ ፡ መለኪያዎች ፡ በተመሳሳይ ፡ ሁኔታዎችም ፡ ልንጠቀምባቸው ፡ እንችላለን ። የጉራጌዎች ፡ የንግድ፡ድር ጅት ፡ እንደ ፡ አንድ ፡ ምሳሌ ፡ ብቻ ፡ ሆኖ ፡ ይቀርባል ።

እላይ ፡ እንደተጠቀሰው ፡ ጉራጌዎች ፡ አብዛኛውን ፡ ንግድ ፡ የሚያካሄዱት ፡ በሽ ርክና ፡ ማህበር ፡ አማካይነት ፡ ነው ። አንድ ፡ ነጋዴ፡ ንግድ፡ ለመጀመር፡ ሲያስብ ፡ ንግዱን

የሚያካሂድለትን ፡ አንድ ፡ ታማኝ ፡ ሰው ፡ ይፈልጋል ። የዚህን ፡ ዓይነት ፡ ሰው ፡ ሲያ ገኝ ፡ አንደኛው ፡ ሥራውን ፡ እንዲያካሂድ ፡ ሁለተኛው ፡ ደግሞ ፡ ገንዘብ ፡ እንዲያ ዋጣ ፡ ተስማምተው ፡ ንግዱን ፡ ይጀምራሉ ። የሚታመን ፡ ሰው ፡ ካልተገኘ ፡ ነጋዴው፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ቀጥሮ ፡ ንግዱን ፡ እንዲያካሂድለት ፡ ያደርጋል ። አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ የዚህ ፡ ዓይነቱ ፡ አቋም ፡ ፍሬያማ ፡ ከሆነ ፡ ሁለቱ ፡ ወገኖች ፡ ተስማምተው ፡ አንድ ፡ የሽርክና ፡ ማሕበር ፡ ያቋቁማሉ ።[2]

ይህን ፡ በመሰለ ፡ ስምምነት ፡ መሠረት ፡ ሁለቱ ፡ ወገኖች ፡ ትርፉንና ፡ ኪሳራ ውን ፡ ይካፈላሉ ። ራሳቸውንም ፡ በአንድነት ፡ የንግድ ፡ ድርጅቱ ፡ ባለቤቶች ፡ እንደ ሆኑ ፡ ይቆጥራሉ ፤ ውሳኔም ፡ አብረው ፡ ለመስጠት ፡ ይችላሉ ። የስምምነቱ ፡ ጊዜ ፡ አልቆ ፡ ብድር ፡ ሁሉ ፡ ከተከፈለ ፡ በኋላ ፡ ያዋጡት ፡ ካፒታል ፡ በዓይነት ፡ ሳይሆን ፡ በዋጋው ፡ መጠን ፡ ይመለስላቸዋል ። ቀሪውንና ፡ የድርጅቱን ፡ ዋጋ ፡ ጭማሪ ፡ ማኅበ ረተኞቹ ፡ በውለታቸው ፡ መሠረት ፡ ይካፈላሉ ። የሆነ ፡ ሆኖ ፡ የተለያዩ ፡ ሁኔታዎች ፡ ሊኖሩ ፡ ይችላሉ ። አንዳንዴ ፡ ሁለቱም ፡ ወገኖች ፡ እኩል ፡ ካፒታል ፡ ሲያዋጡ ፤ አንዳንዴ ፡ ደግሞ ፡ መጠኑ ፡ የተለያየ ፡ ካፒታል ፡ ያዋጣሉ ። የንግዱ ፡ ድርጅት ፡ ትልቅ ፡ ሲሆን ፡ ማኅበረተኞቹ ፡ ከሁለት ፡ ሰዎች ፡ በላይ ፡ ሆነው ፡ ይገኛሉ ። የሆነ ፡ ሆኖ ፡ በእንደዚህ ፡ ዓይነቱ ፡ ሁኔታ ፡ እንኳን ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ መዋጮው ፡ የንግ ድ ፡ ድርጅቱን ፡ የማካሄድ ፡ ጥበብ ፡ ብቻ ፡ ሆኖ ፡ የሚገኝ ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ ይኖራል ።

በጸሐፊው ፡ እምነት ፡ መሠረት ፡ ከላይ ፡ የተገለጠው ፡ የንግድ ፡ አቋም ፡ በንግድ ሕጉ ፡ ውስጥ ፡ ከተጠቀሱት ፡ የሽርክና ፡ ማህበሮች ፡ አንዱ ፡ ስለሆነ ፡ የንግድ ፡ ሕግ ፡ ተፈጻሚ ፡ እንዲሆንበት ፡ ያስፈልጋል ። የንግድ ፡ ሕጉ ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ውልን ፡[3] እንደሚከተለው ፡ ይገልጻል ፡— "የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ውል ፡ ማለት ፡ ሁለት ፡ ወይም ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ መዋጮ ፡ አዋጥተው ፡ በአንድነትና ፡ በሕብረት ፡ የኤኮኖሚ ፡ ተግባር ፡ ያለው ፡ ሥራ ፡ ለመሥራትና ፡ ከሚገኘው ፡ ትርፍም ፡ ሆነ ፡ ከሚመጣው ፡ ዕዳ ፡ ተካ ፋይ ፡ ለመሆን ፡ የሚስማሙበት ፡ ውል ፡ ነው ።"[4] ይህ ፡ ገለጻ ፡ ለጉራጌ ፡ ልማዳዊ ፡ የንግድ ፡ አቋም ፡ መሠረት ፡ የሆኑትን ፡ ነጥቦች ፡ ሁሉ ፡ የያዘ ፡ ነው ።

---

2. እንደዚህ ፡ ዓይነቱ ፡ ከቀጣሪ ፡ ተቀጣሪ ፡ ግንኙነት ፡ ወደ ፡ ሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ግንኙነት ፡ የመለወጡ ፡ ዘዴ ፡ ከመቅጽበት ፡ የሚደረግ ፡ ባይሆንም ፡ የጉራጌዎቹ ፡ ምርጫ ፡ ወደ ፡ ሁለተኛው ፡ የሚያዘነብል ፡ ነው ። ይህ ፡ የሚሆንበትን ፡ ትክክለኛውን ፡ ምክንያት ፡ ለማወቅ ፡ አዳጋች ፡ ቢሆንም ፡ የሽርክናው ፡ ማኅበር፡ ውል፡ የሚይዘውን ፡ መልክ ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፡ ምክንያቱን ፡ በከፊል ፡ ለማጠቃለል ፡ ይቻል ፡ ይሆናል ። እንደዚህ ፡ ያለው ፡ ስምምነት ፡ በልማድ ፡ የሚፈጸመው ፡ በጉርዳ ፡ መልክ ፡ ነው ። ስለ ፡ ጉርዳ ፡ ዝቅ ፡ ብለን ፡ በሰፊው ፡ እንነጋገራለን ። ቢሆንም ፡ ይህ ፡ ቃል ፡ በልማድ ፡ "የወዳጅነት ፡ መተሳሰር" ተብሎ ፡ ይተረጐማል ። በአንደኛው ፡ ወገን ፡ የተወሰደ ፡ ማንኛውም ፡ ዓይነት ፡ የሌላውን ፡ ወገን ፡ ጥቅም ፡ የሚያ ቃውስ ፡ እርምጃ ፡ እንደ ፡ ከባድ ፡ የግዳጅ ፡ ማፍረስ ፡ ተግባር ፡ ተቆጥሮ ፡ ከሰው ፡ አቅም ፡ በላይ ፡ በሆነ ፡ ኃይል ፡ አማካይነት ፡ የቤተ ፡ ሰብ ፡ ሕመምን ፡ የንብረት ፡ ጥፋትንና ፡ ሞትን ፡ የመሳሰሉትን ፡ ቅጣቶች ፡ እንደሚያስከትል ፡ ይታመናል ። እንደዚህ ፡ ያለው ፡ ውል ፡ በቀጣሪውና፡ በተቀጣሪው ፡ መካከል ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ጥብቅነት ፡ ካለው ፡ ቀጣሪው ፡ ነጋዴ ፡ ተቀጣሪውን ፡ የሽርክና ፡ ማኅበርተኛ ፡ ቢያደርግ ፡ የሚያ ገኘውን ፡ ጥቅም ፡ ያሳያል ። በሌላ ፡ መንገድ ፡ ስንመለከተው ፡ ደግሞ ፡ "የወዳጅነት ፡ መተሳሰር" ፡ መኖሩ ፡ ውሉን ፡ በማይተዋወቁ ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ ጥቅም ፡ እንዳይሰጥ ፡ ያደርገዋል ፡ ማለት ፡ ነው ።
3. "የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ውል" ማንኛውም ፡ ዓይነት ፡ የንግድ ፡ ማኅበር ፡ የሚቋቋምበት ፡ ውል ፡ እንጂ ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ብቻ ፡ የሚቋቋምበት ፡ ውል ፡ አይደለም ። የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቍ-፱፻፲ ፡ (፩)ን ፡ ይመለ ከቷል ።
4. ከዚያው ፡ ቍ ፱፻፲፩ ። በፕሮፌሰር ፡ ኤስካራ ፡ የመጀመሪያ ፡ ረቂቅ ፡ ውስጥ ፡ ("የንግድ ፡ ድርጅት") የሚል ፡ አንድ ፡ ትርጉም ፡ ብቻ ፡ ነበረው ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ሕግ ፡ አዘጋጇው ፡ (የፍትሐ ፡ ብሔሩ) ፡ ኮሚሲ ዮን ፡ ማኅበሩን ፡ ማኅበሩ ፡ ከሚመሠረትበት ፡ ውል ፡ ለመለየት ፡ ይህን ፡ ትርጓሜ ፡ ለወጥ ፡ አድርጎታል።

በመጀመሪያ ፡ ተዋዋዮቹ ፡ "በአንድነትና ፡ በሕብረት ፡ --- ለመሥራት"[5] መስማማት ፡ አለባቸው ። ይህም ፡ በንግዱ ፡ ጉዳይ ፡ ሁለቱም ፡ ወገኖች ፡ በእኩልነት ፡ ደረጃ ፡ ተካፋዮች ፡ ለመሆን ፡ ይችላሉ ፡ ማለት ፡ ነው ። አንደኛው ፡ ወገን ፡ እንኳን ፡ የአስተዳዳሪነት ፡ ሥልጣን ፡ ቢሰጠው ፡ ሁለቱም ፡ ወገኖች ፡ በከፍተኛ ፡ ውሳኔዎች ፡ ላይ፡ ተካፋዮች ፡ ይሆናሉ ። ይህ ፡ የንግድ ፡ ይዞታ ፡ ከብድር ፡ ውል ፡ ወይም ፡ ከኪራይ ፡ የተለየ ፡ ነው ። ብድርና ፡ ኪራይ ፡ በከፊል ፡ ከላይ ፡ የተጠቀሰውን ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ውል ፡ ቢመስሉም ፡ አበዳሪውና ፡ አከራዩ ፡ በንግድ ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ያላቸው ፡ ተካፋይነት ፡ የተወሰነ ፡ ነው ።[6] በተጨማሪም ፡ በብድርና ፡ በኪራይ ፡ ጊዜ ፡ ሁለቱ ፡ ወገኖች ፡ ያሉአቸው ፡ ዓላማዎች ፡ የተለያዩ ፡ ናቸው ፤ ይህም ፡ አንደኛው ፡ ወገን ፡ የሌላውን ፡ ፍላጐት ፡ በሚቃረን ፡ መንገድ ፡ የሚሠራበት ፡ ጊዜ ፡ ይኖራል ፡ ማለት ፡ ነው ። በሽርክና ፡ ማሕበር ፡ ግን ፡ ማሕበረተኞቹ ፡ ሁሉ ፡ በሥራው ፡ መካፈልና ፡ ለተመሳሳይ ፡ ግብ ፡ መሥራት ፡ አለባቸው ። የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ውል ፡ ከሥራ፡ ውልም፡ የተለየ ፡ ነው ። ምክንያቱም ፡ የሥራ ፡ ውል ፡ በሠራተኛው ፡ በኩል ፡ የበታችነትን ፡ ስለሚያመለክት ፡ ነው ። በማሕበረተኞች ፡ መካከል ፡ ግን ፡ የበላይነትና ፡ የበታችነት ፡ አቋም ፡ አይገኝም ።[7] ሁለተኛ ፡ ሁሉም ፡ ወገኖች ፡ ለንግዱ ፡ ድርጅት ፡ መዋጮ ማድረግ ፡ አለባቸው ። ከላይ ፡ እንደተመለከተው ፡ በጉራጌዎች ፡ መካከል ፡ አንደኛው ወገን ፡ የካፒታል ፡ መዋጮ ፡ ሲያደርግ ፡ ሁለተኛው ፡ ደግሞ ፡ የአገልግሎት ፡ መዋጮ ያደርጋል ። ሁለቱም ፡ ዓይነት ፡ መዋጮዎች ፡ በንግድ ፡ ሕጉ ፡ የታወቁ ፡ ናቸው ።[8] ሶስተኛ ፡ የድርጅቱ ፡ ግብ ፡ የኤኮኖሚ ፡ ተግባር ፡ ያለውን ፡ ሥራ ፡ መፈጸም ፡ መሆን አለበት ። ከዚህ ፡ በላይ ፡ የጠቀስናቸው ፡ የንግድ ፡ ሥራ ፡ የሚያከናውኑት ፡ የጉራጌ ፡ የ "ሽርክና ፡ ማኅበሮች" የዚሁ ፡ ዓይነት ፡ ተግባር ፡ ያላቸው ፡ መሆናቸው ፡ የማይካድ ፡ ነው ።[9] በመጨረሻ ፡ አንድ ፡ የሽርክና ፡ ማሕበር ፡ ውል ፡ የትርፍንና ፡ የኪሣራን ፡ መካፈል ፡ ጉዳይ ፡ መመልከት ፡ አለበት ። ይህ ፡ በጉራጌ ፡ ድርጅት ፡ ውስጥ ፡ ያለ ፡ ነው ። ይህ ፡ ሕጋዊ ፡ ግንኙነት ፡ "ትርፎችን ፡ ለማግኘት ፡ ወይም ፡ ለመከፋፈል ፡ ሳይሆን"[10] የሚቋቋም ፡ ተራ ፡ ማኅበር ፡ አይደለም ። እዚህ ፡ ላይ ፡ ብድሮች ፡ ኪራዮች ፡ ወይም ፡ የሥራ ፡ ውሎች ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ትርፍን ፡ የሚያከፋፍሉ ፡ ሆነው ፡ ሲገኙ ፡ ኪሣራን ፡ ግን ፡ ዘወትር ፡ የማያከፋፍሉ ፡ መሆናቸውን ፡ መግለጽ ፡ ያስፈልጋል ።

ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተደረገው ፡ ገለጻ ፡ የጉራጌ ፡ የንግድ ፡ ግንኙነቶች ፡ በንግድ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ የተጻፈውን ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ውል ፡ እንደሚመስሉ ፡ ያስረዳል ። ይህ ፡ አስተያየት ፡ ራሳቸውን ፡ እንደ ፡ "ማኅበረተኞች" ፡ ከሚቆጥሩት ፡ ከወገኖቹ ፡

5. አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ "ኢፌክቲዮ ፡ ሶሲታቲስ" ፡ በመባል ፡ ይጠራል ። ኤስካራ ፡ ኩር ፡ ደ ፡ ድሯ ፡ ኰሜርሲያል ፡ (፪ኛ ፡ እትም ፡ ፲፱፻፶፪ ፡ ዓ . ም . እ . ኤ . አ .) ፡ ገጽ ፡ ፫፻፲፪ ፡ ይመለከቷል ።

6. በቂ ፡ ገንዘብ ፡ ለሌላቸው ፡ ኩባንያዎች ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ የገንዘብ ፡ ብድር ፡ በሚሰጥበት ፡ ጊዜ ፡ አበዳሪው ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ኩባንያውን ፡ በመምራት ፡ ረገድ ፡ የተግባር ፡ ተካፋይ ፡ እንደሚሆን ፡ የተረጋገጠ ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ አበዳሪው ፡ እንደ ፡ ሽርክና ፡ ማኅበርተኛ ፡ መቆጠሩ ፡ አጠራጣሪ ፡ ነው ። ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍ . ፭ ፡ የተጠቀሰውን ፡ ኤስካራን ፡ ገጽ ፡ ፫፻፲፪ ፡ ይመለከቷል ።

7. ስለነዚህ ፡ ልዩነቶች ፡ ዝርዝር ፡ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍ . ፭ ፡ የተጠቀሰውን ፡ ኤስካራን ፡ ከገጽ ፡ ፫፻፲ ፡ እስከ ፡ ፫፻፲፫ ፡ ይመለከቷል ።

8. የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቍ . ፪፻፹፱ ፡ (፩) ።

9. አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ በንግድ ፡ ሕግ ፡ ቍ ፭ ፡ እንደ ፡ "ንግድ" ከተገለጹት ፡ ሥራዎች ፡ አንዱን ፡ ወይንም ፡ ከአንድ ፡ የበለጡትን ፡ ሲሠሩ ፡ ይገኛሉ ።

10. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍ ፬፻፩ ። ማኅበሮቹ ፡ የኢኮኖሚ ፡ ተግባር ፡ ያላቸውን ፡ ሥራዎች ፡ በማከናወን ፡ ትርፍ ፡ ለማስገኘት ፡ የተመሠረቱ ፡ አይደሉም ።

ምኞት ፡ ጋራ ፡ የሚስማማ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ድርጅቶቹ ፡ እንደ ፡ ንግድ ፡ ድርጅቶች ፡ በተለይም ፡ እንደ ፡ ሽርክና ፡ ማኅበሮች ፡ መቆጠር ፡ አለባቸው ።[11] ቢሆንም ፡ እነ ዚህ ፡ ማኅበሮች ፡ ሁለት ፡ የንግድ ፡ ሕግ ፡ ድንጋጌዎችን ፡ የማይፈጽሙ ፡ ሆነው ፡ ይገኛሉ ።

በመጀመሪያ ፡ እነዚህ ፡ ውሎች ፡ ቍ ፡ ፲፻፲፬ ፡ በሚያዘው ፡ መሠረት ፡ በጽሑፍ ስለማይፈጸሙ ፡ በንግድ ፡ ሕጉ ፡ መሠረት ፡ ፈራሾች ፡ ናቸው ።[12] ፡ የጉራጌ ፡ የሽር ክና ፡ ማሕበሮች ፡ የሚቋቋሙት ፡ "የቄጥ ፡ ጉርዳ" በሚል ፡ ሥያሜ ፡ በሚታወቅ ፡ ውል፡ነው። (ቀጥተኛ፡ትርጓሜውም፡ "በንግድ ፡ የወዳጅነት ፡ መተሳሰሪያ" ማለት ፡ ነው፡) ይህ ፡ ውል ፡ የሆነውን ፡ ያኸል ፡ እራሱን ፡ የቻለ ፡ ልማዳዊ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓትም ፡ ነው ። በሁለቱም ፡ ወገኖች ፡ ላይ ፡ ግዴታን ፡ ያስከትላል ። ሁለቱ ፡ (ወይም ፡ ከሁለት ፡ በላይ፡ የሆኑ) ወገኖች ፡ በ"ዳኛ" ፡ (ሽማግሌ)[13] ፊት ፡ ደጋግመው ፡ የተሰፉ ፡ ቃሎችን ፡ ይለዋወጣሉ ። ስለ ፡ ውሉ ፡ አፈጻጸም ፡ አለመግባባት ፡ ሲፈጠር ፡ ተዋዋዮቹ ፡ ወደ ፡ ዳኛው ፡ ይሄዳሉ ። ስለዚህ ፡ የሽማግሌው ፡ ሥራ ፡ በምስክርነት ፡ ብቻ ፡ የሚወሰን ፡ አይ ደለም ። ውሉን ፡ በማይፈጽመው ፡ ወገን ፡ ላይ ፡ መቅሰፍት ፡ ይወርዳል ፡ ተብሎ ፡ ይታ መናል ።[14] የዚህ ፡ ዓይነቱ፡በቃል ፡ የሚፈጸም ፡ ውል ፡ የሚገኘው ፡ ምናልባት ፡ በጉራ ጌዎች ፡ ዘንድ ፡ ብቻ ፡ አይደለም ። ለምሳሌ ፡ ያህል ፡ ፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ የሚያትተው ፡ በጽሑፍ ፡ ስለሚፈጸሙ ፡ ውሎች ፡ ሳይሆን ፡ "በሥራ ፡ በአገልግሎት ፡ ወይም ፡ በቃል ፡"[15] ስለሚፈጸሙ ፡ የሽርክና ፡ ማሕበሮች ፡ ነው ። እነዚህ ፡ የሽርክና ፡ ማሕ በሮች ፡ በተጻፈ ፡ ውል ፡ ስላልተቋቋሙ ፡ ፈራሾች ፡ ናቸው ። በፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ውሉ ፡ እንደሌለ ፡ ተቆጥሮ ፡ ተዋዋዮቹ ፡ ከመዋዋላቸው ፡ በፊት ፡ ወደ ፡ ነበ

---

11. እነዚህ ፡ አመዳደቦች ፡ ማንኛውንም ፡ ዓይነት ፡ የተወሰነ ፡ ዋና ፡ ገንዘብ ፡ (ካፒታል) ካለማጠቃለላቸ ውም ፡ ሌላ ፡ የያንዳንዱ ፡ ማኅበርተኛ ፡ አላፊነት ፡ እንደ ፡ አክሲዮን ፡ ማኅበር ፡ (የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቍ ፫፻፬) ፡ ወይም ፡ የተወሰነ ፡ ኃላፊነት ፡ እንዳለው ፡ የግል ፡ ማኅበር ፡ (የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቍ . ፭፻፲) ፡ የተወ ሰነ ፡ አይደለም ። ዓላማው ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ በንግድ ፡ ሕግ ፡ ቍ ፩ ፡ ትርጓሜ ፡ መሠረት ፡ ንግድ ፡ ነክ ፡ ነው ። በዚህም ፡ ምክንያት ፡ ተራ ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ሊሆን ፡ አይችልም ። (የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቍ. ፲፻፲፫) ። በሌላ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ እንደ ፡ እሽሙር ፡ ማኅበር ፡ የማንኛውም ፡ አባል ፡ ማኅበርተኝነት፡ በድብቅ ፡ አይቀመጥም ፡ (የንግድ ፡ ሕግ፡ ቍ . ፲፻፸፱ ፡ (፩)) ። ስለዚህ ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ኅ ብረት ፡ ሽርክና ፡ ማኅበር ፡ መቆጠር ፡ ሲኖርበት ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ደግሞ ፡ ማማሾቹ ፡ ማኅበርተኞች ፡ የተወሰነ ፡ አላፊነት ፡ ሲኖርባቸው ፡ እንደ ፡ ሁለት ፡ ዓይነት ፡ አላፊነት ፡ ያለበት ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ መቆጠር ፡ አለበት ።

12. ቍ . ፲፻፲፬ ፡ "አይጸናም"፡ ይላል ። ይህ ፡ ቃል ፡ "ፈራሽ ፡ ነው" የሚለው ፡ ሐረግ ፡ የሚሰጠውን ፡ ትር ጉም ፡ ይሰጣል ፡ የሚለው ፡ ክርክር ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ ይቀርባል ።

13. ዳኛው ፡ በዚህን ፡ ጊዜ ፡ ይህንን ፡ ጉርዳ ፡ ለምን ፡ ትፈልጋላችሁ ፡ በማለት ፡ ጥያቄ ፡ ያቀርባል ። ሁለቱም፡ ወገኖች ፡ "ሽርክና ፡ እንዲኖረን" ብለው ፡ ይመልሳሉ ። ዳኛው ፡ ቀጠል ፡ አድርጎ ፡ "ይኼ፡ የአርጀርና፡ የወርቲን ፡ ጉርዳ ፡ ነው" ይላል ። (አርጀርና ፡ ወርቲን ፡ የጉርዳን ፡ ውል ፡ የተዋዋሉ ፡ ሰዎች ፡ ናቸው) ። ሁለቱም ፡ ወገኖች ፡ መልሰው ፡ ይህንኑ ፡ ይናገራሉ ። ደግሞ ፡ በተጨማሪ ፡ ዳኛው ፡ "ይህንን ፡ ጉርዳ ፡ ያፈረሳችሁ ፡ እንደሆን ፡" ሲል ፡ ሁለቱም ፡ ወገኖች ፡ "በመስቀል ፡ ቀን ፡ ቡትቶ ፡ ለብሼ ፡ ቅርጫት ፡ ተሸክሜ ፡ እርስዎ ፡ ቤት ፡ (ዳኛው፡ ቤት) ልመና፡ እንድመጣ፡ ያድርገኝ" ይላሉ። እነዚህን፡ ጥያቄዎችና ፡ መልሶች ፡ ሶስት ፡ ጊዜ ፡ ይደጋግማሉ ። በመጨረሻም ፡ ዳኛው ፡ "ጉርዳው ፡ ውላችሁን ፡ ከማፍረስ፡ ይጠብቃችሁ" በማለት ፡ መርቆ ፡ ያሰናብታቸዋል ።

14. ማስታወሻ ፡ ቍ . ፱ን ፡ ከላይ፡ ይመለከቷል ። በተጨማሪም ፡ ከዊልያም ፡ ኤ ሻክ፡ የተደረሰ ፡ ዘ ፡ ጉራጌ ፡ የሚለውን ፡ በኦክስፎርድ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ ፕሬስ ፡ በ፲፱፻፷፮ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የታተመ ፡ መጽሐፍ ፡ ይመለከ ቷል። "የቄጥ ፡ ጉርዳ" ለከፍተኛ ፡ የንግድ ፡ ውሎች ፡ ማለት ፡ እንደ ፡ መሬት ፡ ሽያጭ ፡ ላሉ ፡ ውሎች ፡ የሚጠቅም ፡ ነው ። በተጨማሪም ፡ በነፍስ ፡ ግዳይ ፡ ጊዜ ፡ እርቅ ፡ የሚደረግበት ፡ "የደም" ወይም ፡ "የአንጀት" ጉርዳ ፡ እና ፡ ሁለቱ ፡ ወገኖች ፡ አንዱ ፡ በሌላው ፡ ላይ ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ ቢሆን ፡ ጉዳት ፡ እንዳያደርስ ፡ ቃል ፡ የሚገቡበት ፡ "የርብረት" ፡ ጉርዳ ፡ አሉ ።

15. ፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ ምዕራፍ ፡ ፴፩ ።

ሩበት ፡ ሁኔታ ፡ እንዲመለሱ ፡ መደረግ ፡ አለበት ። ቢሆንም ፡ የ"ሽርክና ፡ ማኅበሮቹ" አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ለረጅም ፡ ጊዜ ፡ ሲሠሩ ፡ የቆዩ ፡ ሆነው ፡ ይገኛሉ ። በዚህን ፡ ጊዜ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ የውል ፡ ፈራሽነት ፡ ደንቦች ፡ የተወሳሰበውን ፡ ሁኔታ ፡ አጥ ብቀው ፡ መመልከት ፡ አለባቸው ።

ሁለተኛው ፡ ደግሞ ፡ እነዚህ ፡ የሽርክና፡ማኅበሮች፡ቁ ፡ ፪፻፲፱ ፡ በሚያዘው ፡ መሠ ረት ፡ በማስታወቂያ ፡ የወጡና ፡ የተመዘገቡ ፡ አይደሉም ። የንግድና ፡ ኢንዱስትሪ ፡ ሚኒስቴር ፡ የንግድ ፡ ድርጅቶች ፡ እንዲመዘገቡ ፡ ጥረት ፡ አድርጎ ፡ ነበር ። በዚሁ ፡ መሠረት ፡ አሁን ፡ በአዲስ ፡ አበባ ፡ አሥር ፡ ሺ ፡ የንግድ ፡ ድርጅቶች ፡ ተመዝግበው ፡ ይገኛሉ ። ከነዚህ ፡ መካከል ፡ አራት ፡ መቶዎቹ ፡ የሽርክና ፡ ማኅበሮች ፡ ናቸው ።[16] ይህ ፡ ቍጥር ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ካሉት ፡ የሽርክና ፡ ማኅበሮች ፡ ቍጥር ፡ በጣም ፡ ያነሰ ፡ ነው ። ይህ ፡ የሚሆንበት ፡ ምክንያት ፡ ነጋዴዎች ፡ ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ በማኅበርተኛነት ሳይሆን ፡ በግል ፡ ስማቸው ፡ ስለሚመዘገቡ ፡ ነው ። የመመዝገብ ፡ ሥርዓት ፡ በኢትዮ ጵያ ፡ አዲስ ፡ ነገር ፡ ስለሆነ ፡ ሙሉ ፡ በሙሉ ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ለማዋል ፡ ጊዜን ፡ ይጠይ ቃል ።[17] የንግድ ፡ ድርጅቶችን ፡ አለማስመዝገብ ፡ በቍ ፡ ፪፻፳፫ ፡ እንደሚከተለው ፡ የተጻፈውን ፡ ውጤት ፡ ያስከትላል ፡- "አንድ ፡ የንግድ ፡ ማኅበር ፡ መኖሩም ፡ የሕግ ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ የተሰጠው ፡ መሆኑም ፡ በሕግ ፡ አይታወቅለትም ።"

የንግድ ፡ ማኅበር ፡ ውልን ፡ በጽሑፍ ፡ አለማድረግ ፡ ወይም ፡ የንግድ ፡ ማኅበ ሩን ፡ አለማስመዝገብ ፡ የሚያስከትለውን ፡ ውጤቶች ፡ መመርመር ፡ የዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ ዓላማ ፡ ነው ። የጽሑፉ ፡ መሪ ፡ አሳብ ፡ ማኅበሮቹን ፡ እንደ ፡ ንግድ ፡ ሕግ ፡ የሽርክና ፡ ማሕበሮች ፡ መቁጠርና ፡ የሕጉን ፡ ድንጋጌዎች ፡ በሙሉ ፡ ባለመፈጸማቸው ፡ ከሌሎች ፡ የሽርክና ፡ ማኅበሮች ፡ ጥቂት ፡ ለየት ፡ አድርጎ ፡ መመልከት ፡ ነው ። "በሕግ ፡ ሳይታ ወቍ ፡ የሚሠሩ" ("ዲ ፡ ፋክቶ") የሽርክና ፡ ማኅበሮች ፡ ብለን ፡ ልንሰይማቸው ፡ እን ችላለን ። በጽሑፍ ፡ ያልተደረገ ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ውል ፡ ስለማይመዘገብ ፡ በመ ጀመሪያ ፡ የምንነጋገረው ፡ ስላልተመዘገቡ ፡ "በሕግ ፡ ሳይታወቁ ፡ የሚሠሩ" ፡ ("ዲ ፡ ፋክቶ") የንግድ ፡ ማኅበሮች ፡ ሕጋዊ ፡ ሁኔታ ፡ ነው ። ቀጥለን ፡ በጽሑፍ ፡ ስላልተደ ረገ ፡ የሽርክና ፡ ማህበር ፡ ውል ፡ ውጤት ፡ እንነጋገራለን ።

> ቍ ፡ ፪፻፳፫ ፡ "በመዝገብ ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ መግባት ፡ የተደነገጉት ፡ የዚህ ፡ ሕግ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ተጠናቅቀው ፡ እስኪፈጸሙና ፡ መመዝገቡም ፡ በዚ ህ ፡ ሕግ ፡ ቍ ፹፯ ፡ መሠረት ፡ ታትሞ ፡ እስኪመጣ ፡ ድረስ ፡ አንድ ፡ የንግ ድ ፡ ማኅበር ፡ መኖሩም ፡ በሕግ ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ የተሰጠው ፡ መሆ ኑም ፡ በሕግ ፡ አይታወቅለትም ።"

<u>በሕግ ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ ስለ ፡ መስጠት ፡—</u> በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግና ፡ በን ግድ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ የመብትና ፡ የግዴታ ፡ ባለቤቶች ፡ ሊሆኑ ፡ የሚችሉት ፡ "ሰዎች" ብቻ ፡ ናቸው ። ቢሆኑም ፡ በሕጎቹ ፡ ውስጥ ፡ "ሰዎች" ተብለው ፡ የሚጠሩት ፡ ሰብ አዊ ፡ ፍጡሮች ፡ ብቻ ፡ አይደሉም ። ሕጉ ፡ ለድርጅቶችም ፡ የሰውነት ፡ አቋም ፡ ሰጥ ቷቸዋል ። ለምሳሌ ፡ መንግሥት ፡ እንደ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ተቆጥሮ ፡ የመብቶችና ፡ የግ ዴታዎች ፡ ባለቤት ፡ ተደርጓል ።[18] እነዚህ ፡ ድርጅቶች ፡ የሰውነት ፡ አቋም ፡ የተሰጣ

---

16. ከ፪፻ ፡ የአክስዮን ፡ ማኅበሮች ፡ ከ፬፻ ፡ ኃላፊነታቸው ፡ የተወሰነ ፡ የግል ፡ ማኅበሮችና ፡ ከ፱፻ ፡ የግል ፡ የንግድ ፡ ድርጅቶች ፡ ጋራ ፡ ሲነጣጠር ።

17. የሽርክና ፡ ማኅበሮችን ፡ የመመዝገብ ፡ ጽንሰ ፡ አሳብ ፡ በመጀመሪያ ፡ የተወረሰው ፡ ከ፲፱፻፴፫ ፡ ዓመተ ፡ ምሀረት ፡ የኩባንያዎች ፡ ሕግ ፡ ነው ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ እነዚህ ፡ ድንጋጌዎች ፡ አልተሰራባቸውም ።

18. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍ. ፫፻፺፬ ።

ቸው ፡ በሕጉ ፡ አማካይነት ፡ ስለሆነ ፡ "ሕጋዊ" ሰዎች ፡ ተብለው ፡ ይጠራሉ ። የሽር ክና ፡ ማኅበርም ፡ የንግድ ፡ ሕግ ፡ የሚያዘውን ፡ ፈጽሞ ፡ ሲገኝ ፡ ሕጋዊ ፡ ሰው፡ነው ።[19] በዚህም ፡ ምክንያት ፡ የሽርክናው ፡ ማኅበር ፡ ከማኅበረተኞቹ ፡ የተለየ ፡ አንድ ፡ ፍጡር፡ ይሆናል ። የንብረት ፡ ባለቤት ፡ መሆንንና ፡ ንብረትን ፡ መሸጥና ፡ መለወጥ ፡ የመሰሉ ትን ፡ ተግባሮች ፡ እንደ ፡ ሰዎች ፡ ሆኖ ፡ ሊፈጽም ፡ ይችላል ።

ለሽርክና ፡ ማኅበሮች ፡ የሰውነት ፡ አቋምን ፡ የመስጠት ፡ ተግባራዊ ፡ ጥቅም ፡ የሚታወቀው ፡ ማሕበሩ ፡ በሚፈርስበትና ፡ ሒሳብ ፡ በሚጣራበት ፡ ወቅት ፡ ነው ።[20] ማኅበሩ ፡ አንድ ፡ እራሱን ፡ የቻለ ፡ ሰው ፡ ስለሆነ ፡ የንብረቱ ፡ ባለቤት ፡ የሚሆነው ፡ ማኅበሩ ፡ እንጂ ፡ ማሕበርተኞቹ ፡ አይደሉም ። ከማሕበሩ ፡ ጋር ፡ የንግድ ፡ ግንኙነት ፡ የሚያደርጉ ፡ ሰዎች ፡ የማሕበሩ ፡ ባለ ፡ ገንዘቦች ፡ ወይም ፡ ባለ ፡ ዕዳዎች ፡ ይሆናሉ ። ባለ ፡ ገንዘቦች ፡ ገንዘባቸውን ፡ በመጨረሻ ፡ ከማኅበርተኞቹ ፡ የመጠየቅ ፡ መብት ፡ ቢኖራቸውም ፤ ገንዘባቸው ፡ እንዲከፈላቸው ፡ በመጀመሪያ ፡ መጠየቅ ፡ ያለባቸው ፡ ማኅበሩን ፡ እንጂ ፡ ማኅበርተኞችን ፡ አይደለም ።[21]

ዕዳውን ፡ ለመክፈል ፡ በቂ ፡ ንብረት ፡ ያለው ፡ የአንድ ፡ የሽርክና ፡ ማሕበር ፡ ሂሳብ ፡ በሚጣራበት ፡ ጊዜ ፡ ባለገንዘቦች ፡ መጀመሪያ ፡ ከማሕበሩ ፡ ንብረት ፡ ይከፈ ላሉ ።[22] ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ለማሕበረተኞች ፡ የመጀመሪያው ፡ መዋጮ ፡ ዋጋ ፡ ታስቦ ፡ ይከፈላቸዋል ። (ያዋጡት ፡ ንብረት ፡ እራሱ ፡ እንዲመለስላቸው ፡ ለማድረግ ፡ አይ ችሉም) ።[23] ይህ ፡ ከተፈጸመ ፡ በኋላ ፡ ቀሪ ፡ የሚሆነው ፡ ትርፍ ፡ ተብሎ ፡ ሌላ ፡ ስም ምነት ፡ ከሌለ ፡ በተቀር ፡ ለማኅበረተኞቹ ፡ በትክክል ፡ ይከፈላል ።[24] የማኅበሩ ፡ ንብ ረት ፡ ግን ፡ በቂ ፡ በማይሆንበት ፡ ጊዜ ፡ ሂሳብ ፡ አጣሪዎች ፡ ማሕበርተኞቹ ፡ መዋጮ፡ በማድረግ ፡ ባለገንዘቦችን ፡ እንዲከፍሉ ፡ ለማድረግ ፡ ይችላሉ ።[25]

በዚህ ፡ የአከፋፈል ፡ ተራ ፡ ዋናው ፡ ነገር ፡ ሕጉ ፡ የማኅበሩ ፡ ባለገንዘቦች ፡ ከማ ሕበረተኞች ፡ በፊት ፡ እንዲከፈሉ ፡ ማድረጉ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ባለገንዘቦች ፡ ከማኅበረ ተኞችና ፡ በማኅበረተኞችም ፡ በኩል ፡ ከሚጠየቁ ፡ ሰዎች ፡ ቅድሚያ ፡ ተሰጥቶአቸ ዋል ። ይህ ፡ ቀደምትነት ፡ የተመሠረተው ፡ የማኅበሩን ፡ የተለየ ፡ ሕጋዊ ፡ ሰውነት ፡ በሚፈጥር ፡ አሳብ ፡ ላይ ፡ ነው ። በዚህ ፡ ምክንያት ፡ የማሕበሩ ፡ ባለገንዘቦች ፡ ከማኅ በረተኞቹ ፡ የግል ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ ቀድመው ፡ ከማኅበሩ ፡ ንብረት ፡ ለመካ ፈል ፡ መብት ፡ አላቸው ። ያንድ ፡ ማኅበርተኛ ፡ የግል ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂ ፡ ከማኅበሩ ፡ ንብረት ፡ እንዲከፈለው ፡ በቀጥታ ፡ ለመጠየቅ ፡ መብት ፡ የለውም ። ሊከፈል፡ የሚችለው፡ ከባለዕዳው ፡ ማኅበርተኛ ፡ ንብረት ፡ ነው ። ይህም ፡ ንብረት ፡ ማኅበረተኛው ፡ በማኅበሩ ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ ንብረት ፡ የሚጨምር ፡ ነው ። በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ከላይ ፡ እንደተገ ለጸው ፡ የአንድ ፡ ማሕበረተኛ ፡ የግል ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂ ፡ ከማኅበሩ ፡ ንብረት ፡ እንዲ ከፈለው ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ፤ ነገር ፡ ግን ፡ የማኅበሩ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ በአከፋ ፈል ፡ ቅድሚያ ፡ ስለሚሰጣቸው ፡ የግል ፡ ባለገንዘቦች ፡ የሚከፈሉት ፡ የማኅበሩ ፡ ገን

---

19. የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቍ. ፪፻፲ ፡ (፪) ።
20. ጂ፡ ሪፔር ፡ ትሬቴ፡ ኤሌሜንቴር፡ ደ ፡ ድሯ፡ ኰሜርሲያል ፡ (፫ኛ ፡ እትም ፡ ፲፱፻፶፬) ፡ ገጽ ፡ ፪፻፳፰ ።
21. የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቍ. ፪፻፹፬ ።
22. የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቍ. ፪፻፹፰ ። ማኅበረተኞች ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ ከሆኑ ፡ ገንዘባቸው ፡ ይከፈላቸዋል ፡ ግን ፡ ሶስተኛ ፡ ወገኖች ፡ ከተከፈላቸው ፡ በኋላ ፡ ነው ።
23. የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቍ. ፪፻፹፱ ።
24. የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቍ. ፪፻፺ ፡ (፩) (፫) ።
25. የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቍ. ፪፻፹፰ ፡ (፩) ።

ዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ ከተከፈሉ ፡ በኋላ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ የግል ፡ ባለገንዘብ ፡ መጠየቅ ፡ የሚችለው ፡ ንብረት ፡ ባለዕዳው ፡ ማሕበርተኛ ፡ በማኅበሩ ፡ ውስጥ ፡ ባለው ፡ ንብረት ፡ መጠን ፡ ነው ።

ለምሳሌ ፡ ሀ ፡ ለ ፡ እና ፡ ሐ ፡ ከቍጥር ፡ ፪፻፳፫ ፡ እና ፡ በጠቅላላው ፡ ከንግድ ፡ ሕግ ፡ ጋር ፡ ተስማሚ ፡ የሆነ ፡ የኀርክና ፡ ማኅበር ፡ ያቋቁሙ ። ሀ ፡ በማኅበሩ ፡ ስም ፡ ከመ ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ ሺ ፡ ብር ፡ ይበደራል ። አሁን ፡ ባለዕዳው ፡ ማኅበሩ ፡ እንጂ ፡ ሀ ፡ ለ ፡ ወይም ፡ ሐ ፡ አይደሉም ። መ ፡ እንዲከፈል ፡ ለመጠየቅ ፡ የሚችለው ፡ ከማኅበሩ ፡ ንብረት ፡ ነው ። በተጨማሪ ፡ በምሳሌአችን ፡ ውስጥ ፡ ሀ ፡ ከሠ ፡ ላይ ፡ በራሱ ፡ ስም ፡ አንድ ፡ ሺ ፡ ብር ፡ ተበድሯል ፡ እንበል ። ሀ ፡ በማኅበሩ ፡ ውስጥ ፡ ካለው ፡ ንብረት ፡ በስተቀር ፡ ሌላ ፡ ሃብት ፡ የለውም ። መ ፡ ከማኅበሩ ፡ ላይ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂ ፡ እንደመ ሆኑ ፡ መጠን ፡ የሚከፈለው ፡ ለማኅበርተኞቹ ፡ ንብረቱ ፡ ከመከፋፈሉ ፡ በፊት ፡ ነው ። ሠ ፡ በማኅበሩ ፡ ውስጥ ፡ ካለው ፡ የሀ ፡ ንብረት ፡ እንዲከፈለው ፡ ሊጠይቅ ፡ ይችላል ። ሆኖም ፡ ሠ ፡ በዚህን ፡ ጊዜ ፡ የሚጠቀመው ፡ በሀ ፡ መብት ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ሠ ፡ የሚ ከፈልው ፡ መ ፡ ከተከፈለ ፡ በኋላ ፡ ነው ። በዚህ ፡ ምክንያት ፡ መ ፡ ከተከፈለ ፡ በኋላ ፡ የማኅበሩ ፡ ንብረት ፡ ካለቀ ፡ ሠ ፡ ሳይከፈል ፡ ይቀራል ። ቀሪ ፡ ንብረት ፡ ካለ ፡ ግን ፡ ሠ ፡ የሚከፈለው ፡ ሀ ፡ ከሚያገኘው ፡ የንብረት ፡ ክፍያ ፡ ውስጥ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ማሕበሩ፡ የሶስት ፡ ሺ ፡ ብር ፡ ንብረት ፡ ቢኖረው ፡ መ ፡ በመጀመሪያ ፡ ሺ ፡ ብሩን ፡ ይከፈላል ። ቀሪው ፡ ሁለት ፡ ሺ ፡ ብር ፡ በማኅበረተኞች ፡ መካከል ፡ ይከፋፈላል ። ሌላ ፡ ስምምነት ከሌለ ፡ በስተቀር ፡ ሶስቱ ፡ ማኅበረተኞች ፡ ከሁለቱ ፡ ሺ፡ብር፡ሲሶ ፡ ሲሶ፡ይደርሳቸዋል ። ይኸውም ፡ ለያንዳንዱ ፡ ስድስት ፡ መቶ ፡ ስልሳ ፡ ስድስት ፡ ብር ፡ ማለት ፡ ነው ። በዚህ፡ አከፋፈል ፡ ሀ ፡ የሚያገኘው ፡ ስድስት ፡ መቶ ፡ ስልሳ ፡ ስድስት ፡ ብር ፡ ብቻ ፡ ስለሆነ ፡ ሠ ፡ የሚያገኘውም ፡ በዚሁ ፡ መጠን ፡ ብቻ ፡ ነው ።

<u>ሕጋዊ ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ እጦት ፡</u>— በቍ. ፪፻፳፫ ፡ እንደተመለከተው ፤ አንድ የኀርክና ፡ ማሕበር ፡ ሕጋዊ ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ አይኖረውም ፡ ማለት ፡ ማኅበሩ ፡ ከማኅበረተኞቹ ፡ የተለየ ፡ ሆኖ ፡ አይቆጠርም ፡ ማለት ፡ ነው ። ይህም ፡ ሁለት ፡ መልክ፡ ያለው ፡ ውጤትን ፡ ያስከትላል ። ለማኅበሩ ፡ ንብረት ፡ ባለቤት ፡ የሚሆን ፡ ሕጋዊ ፡ ሰው ፡ ስለሌለ ፤ የንብረቱ ፡ ባለቤቶች ፡ ማኅበረተኞቹ ፡ ይሆናሉ ። ሁለተኛ ፡ ደግሞ ፡ ሶስተኛ ፡ ወገኖች ፡ ከማኅበሩ ፡ ጋር ፡ ቀጥተኛ ፡ ግንኙነት ፡ ስላላደረጉ ፤ ገንዘብ ፡ ለመ ጠየቅ ፡ የሚችሉት ፡ ከማኅበረተኞቹ ፡ ነው ።

በምሳሌ ፡ ለመግለጽ ፡ ሀ ፡ ለ ፡ እና ፡ ሐ ፡ ቍ ፡ ፪፻፳፫ ፡ የሚያዘውን ፡ ሳይፈጽሙ ፡ አንድ ፡ የኀርክና ፡ ማሕበር ፡ አቋቋሙ ፡ እንበል ። ሀ ፡ በማኅበሩም ፡ ስም ፡ ሳደረገው ፡ የንግድ ፡ መለዋወጥ ፡ ማኅበሩ ፡ ለ መ ፡ የአንድ ፡ ሺ ፡ ብር ፡ ባለዕዳ ፡ ይሆናል ። ማሕ በሩ ፡ ሕጋዊ ፡ ሰው ፡ ሆኖ ፡ ቢቋቋም ፡ ኖሮ ፡ መ ፡ ገንዘቡን ፡ ከማኅበሩ ፡ ለመጠየቅ ፡ በቻለ ፡ ነበር ። በምሳሌያችን ፡ ውስጥ ፡ ግን ፡ ማኅበሩ ፡ ሕጋዊ ፡ ሰው ፡ ለመሆን ፡ አል በቃም ፡ ስላልን ፤ መ ፡ ገንዘቡን ፡ ለመጠየቅ ፡ የሚችለው ፡ ከሀ ፡ ከለ ፡ እና ፡ ከሐ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ እያንዳንዱ ፡ ማኅበርተኛ ፡ ሶስት ፡ መቶ ፡ ሰላሳ ፡ ሶስት ፡ ብር ፡ የመክ ፈል ፡ ግዴታ ፡ ይኖርበታል ።

አሁን ፡ ደግሞ ፡ ሕጋዊ ፡ ሰውነትን ፡ የተነፈገው ፡ ማኅበር ፡ ሂሣቡን ፡ ሲያጣራ ፡ ምን ፡ እንደሚሆን ፡ እንመልከት ። እያንዳንዱ ፡ ማኅበረተኛ ፡ የንብረቱ ፡ ባለቤት ፡ ስለ ሆነ ፡ ንብረት ፡ የማከፋፈል ፡ ጉዳይ ፡ ሊነሳ ፡ አይችልም ። እያንዳንዱ ፡ ማሕበረተኛ ፡ የመዋጮውን ፡ ዋጋ ፡ ይሰጣል ። ተቃራኒ ፡ ስምምነት ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ ከዚህ ፡ የቀረው ትርፍ ፡ ሆኖ ፡ ለማኅበረተኞቹ ፡ በትክክል ፡ ይከፈላል ። የማኅበሩ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂ ዎች ፡ ገንዘባቸው ፡ ከማሕበረተኞቹ ፡ ንብረት ፡ እንዲከፈላቸው ፡ ለማድረግ ፡ ይች

ላሉ ። የሰውነት ፡ መብት ፡ መነፈግ ፡ ሆን ፡ ለን ፡ እና ፡ ሐን ፡ ለመቅጣት ፡ የታሰበ ፡ እንጂ ፡ ከማኅበሩ ፡ ገንዘብ ፡ የሚጠይቁትን ፡ እንደ ፡ መ ፡ በቅን ፡ ልቡና ፡ ያሉትን ፡ ሶስተኛ ፡ ወገኖች ፡ ለመቅጣት ፡ የታቀደ ፡ አይደለም ። ስለዚህ ፡ ባሁኑ ፡ ምሳሌ ፡ መ ፡ ማኅበሩን ፡ በቀጥታ ፡ ለመክሰስ ፡ ከፈለገ ፡ እንዲፈቀድለት ፡ ያስፈልጋል ። በሌላው ፡ በኩል ፤ መ ፡ ማኅበረተኞቹን ፡ በቀጥታ ፡ለመጠየቅ ፡ ይችላል ። በአንደኛውም ፡ ሆነ በሁለተኛው ፡ መንገድ ፤ መ ፡ ጠቅላላ ፡ ገንዘቡ ፡ ከተገኘው ፡ ንብረት ፡ እንዲከፈለው ፡ ለማድረግ ፡ ይቻላል ።

የሕጋዊ ፡ ሰውነት ፡ መብት ፡ እጦትም ፡ ትርጉም ፡ ግልጽ ፡ ሆኖ ፡ የሚታየው ፡ ከማኅበረተኞቹ ፡ ገንዘብ ፡ የሚጠይቁ ፡ ሰዎች ፡ በሚኖሩበት ፡ ጊዜ ፡ ነው ። ወደ ፡ ምሳሌያችን ፡ እንመለስና ፡ ሀ ፡ በራሱ ፡ ስም ፡ ከሠ ፡ አንድ ፡ ሺ ፡ ብር ፡ ተበድሯል ፡ እንበል ። እላይ ፡ ማኅበሩ ፡ ሕጋዊ ፡ ሰውነት ፡ ሲሰጠው ፡ ከማሕበሩ ፡ ገንዘብ ፡ የሚጠይቁ ፡ ክፍሎች ፡ እንደ ፡ ሠ ፡ ካሉት ፡ ሰዎች ፡ ያከፋፈል ፡ ቅድሚያ ፡ እንደሚሰጣቸው ፡ አይተናል ። ሕጋዊ ፡ ሰውነት ፡ በሌለ ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ "በማኅበሩ ፡ ስም ፡ የተያዘ ፡ ንብረት" እንደሌለ ፡ አይተናል ። ስለዚህ ፡ ከማኅበሩ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎችና ፡ ከማኅበረተኞቹ ፡ የግል ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ ገንዘባቸውን ፡ ለመካፈል ፡ የሚችሉት ፡ ከማኅበርተኞቹ፡ ንብረት ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ በምሳሌአችን ፡ ውስጥ ፡ መ ፡ የተባለው ፡ የማሕበሩ ፡ ባለገንዘብ ፡ እንዲከፈል ፡ መጠየቅ ፡ የሚችለው ፡ ከማኅበረተኞቹ ፡ ንብረት ፡ ብቻ ፡ ነው ። መ ፡ ከሚጠየቀውም ፡ ገንዘብ ፡ ገሚሱ ፡ የሚከፈለው ፡ ከሀ ፡ ንብረት ፡ ውስጥ ፡ ነው። ሠም ፡ ከሀ ፡ ንብረት ፡ ለመከፈል ፡ ተመሳሳይ ፡ መብት ፡ አለው ። ሠ ፡ ለማኅበሩ ፡ ሕጋዊ ፡ ሰውነት ፡ አለመኖር ፡ ኃላፊ ፡ ስላልሆነ ፡ በዚህ ፡ ሁኔታ ፡ ለመጠቀም ፡ ይችላል ። "ማኅበሩ" የሶስት ፡ ሺ ፡ ብር ፡ ንብረት ፡ አለው ፡ ብለን ፡ እናስብ ። በሕጋዊ ፡ ሰውነት ፡ አለመኖር ፡ ምክንያት ፡ ግን ፡ ትርጉሙ ፡ እያንዳንዱ ፡ ማሕበረተኛ ፡ አንድ ፡ ሺ ፡ ብር ፡ አለው ፡ ማለት ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ሀ ፡ የአንድ ፡ ሺ ፡ ብር ፡ ንብረት ፡ አለው ማለት ፡ ነው ። መ ፡ ከያንዳንዱ ፡ ማኅበረተኛ ፡ የገንዘቡ ፡ አንድ ፡ ሶስተኛ ፡ እንዲከፈለው ፡ ለመጠየቅ ፡ ስለሚችል ፡ ከሀ ፡ ላይ ፡ ሶስት ፡ መቶ ፡ ሰላሳ ፡ ብር ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ። ሠ ፡ ደግሞ ፡ ከሀ ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ ሺ ፡ ብር ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ። ሀ ፡ ሌላ፡ ንብረት ፡ ከሌለው ፡ ሠ ፡ ከሀ ፡ ላይ ፡ የሚቀበለው ፡ የዕዳውን ፡ ሶስት ፡ አራተኛ ፡ ወይም ሰባት ፡ መቶ ፡ ሃምሳ ፡ ብር ፡ ነው ። መ ፡ ደግሞ ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ ሃምሳ ፡ ብር ፡ ይቀበላል ።(ባለፈው ፡ ምሳሌያችን ፡ ሠ ፡ ስድስት ፡ መቶ ፡ ሰላሳ ፡ ስድስት ፡ ብር ፡ እንደሚያገኝ ፡ አይተን ፡ ነበር ።)

<u>የሽርክና ፡ ማኅበሮች ፡ ይመዝገቡ ፡ የተባለበት ፡ ምክንያት ፡</u> — እስካሁን ፡ ድረስ ስለ ፡ ቍ ፡ ፪፻፳፫ ፡ ያቀረብነው ፡ አስተሳሰብ ፡ ትክክልነት ፡ እንዳለው ፡ ለማረጋገጥ ፡ ሕግ ፡ አውጭው ፡ ክፍል ፡ ቍ ፪፻፳፫ን ፡ ሲደነግግ ፡ የነበረውን ፡ አሳብ ፡ ማወቅ ፡ ያስፈልጋል ።

አንድ ፡ የሽርክና ፡ ማኅበርን ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ መንፈግ ፡ የሚያስከትለው ፡ የመጀመሪያው ፡ ውጤት ፡ ለግል ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ እና ፡ ከማኅበሩ ፡ ገንዘብ ፡ ለሚጠይቁት ፡ ሰዎች ፡ በአከፋፈል ፡ ረገድ ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ ደረጃ ፡ መስጠት ፡ ነው ። ይህ ውጤት ፡ የደረሰው ፡ ማኅበረተኞች ፡ ማኅበሩን ፡ ባለማስመዝገባቸውና ፡ ባለማስታወቃቸው ፡ ስለሆነ ፡ ማኅበሮች ፡ ይመዝገቡ ፡ የሚለው ፡ ደንብ ፡ ግላዊ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎችን ፡ ከማሕበሩ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ አብልጦ ፡ ለመጠበቅ ፡ የተደነገገ ፡

ይመስላል ።[26] የማኅበሮች ፡ አለመመዝገብ ፡ ግላዊ ፡ ባለገንዘቦችን ፡ አብልጦ ፡ የሚጐዳ፡ ይመስላል ፥ ቢሆንም ፡ አስቀድመን ፡ ይህ ፡ አስተያየት ፡ ትክክለኛ ፡ መሆኑን ፡ መመ ርመር ፡ አለብን ።

ከሽርክናው ፡ ማኅበር ፡ ጋር ፡ ግንኙነት ፡ የሚያደርጉ ፡ ሰዎች ፡ የማኅበሩ ፡ መመ ዝገብና ፡ በማስታወቂያ ፡ መውጣት ፡ ሊጠቅማቸው ፡ ይችላል ፥ ምክንያቱም ፡ የሚፈ ልጉትን ፡ መረጃ ፡ አለብዙ ፡ ችግር ፡ ከንግድ ፡ መዝገቡ ፡ ለማግኘት ፡ ስለሚችሉ ፡ ነው ። ለምሳሌ ፥ ማኅበሩ ፡ በእርግጥ ፡ መኖሩን ፥ ማኅበረተኞቹ ፡ እነማን ፡ እንደሆ ኑና ፡ የመዋጮአቸውን ፡ ዋጋ ፡ ከንግድ ፡ መዝገብ ፡ ለማግኘት ፡ ይችላሉ ።[27] እንዲሁም ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ከአንድ ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡[28] ጋር ፡ ግንኙነት ፡ ሲያደርግ ፡ ግንኙነ ቱን ፡ የሚፈጽመው ፡ ባንድ ፡ ሰው ፡ አማካይነት ፡ ስለሆነ ፡ የዚህን ፡ ሰው ፡ ሥልጣን ፡ ማወቅ ፡ በጣም ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ። የኅብረት ፡ ሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ሥራ ፡ አስኪያጆች ፡ ሥልጣን ፡ የሚወሰነው ፡ በማኅበሩ ፡ የሥራ ፡ ግብ ፡ መጠን ፡ ነው ።[29] የማኅበሩ ፡ የሥራ ፡ ግብ ፡ የሚገኘው ፡ በንግድ ፡ መዝገብ ፡ ውስጥ ፡ ነው ።[30] ይህን ፡ ሰፋ ፡ ያለ ፡ ሥልጣን ፡ የሚወስን ፡ ነገር ፡ ቢኖር ፡ ዋጋ ፡ የሚኖረው ፡ በንግድ ፡ መዝገብ ፡ ውስጥ ፡ ሲሰፍር ፡ ወይም ፡ ሶስተኛ ፡ ወገኖች ፡ ማወቃቸው ፡ ሲረጋገጥ ፡ ነው ።[31] ይህ ፡ ደንብ ፡ በይበልጥ ፡ የሚረዳው ፡ ማኅበሩን ፡ ነው ፥ ምክንያቱም ፤ ሶስተኛ ፡ ወገኖች ፡ ባያውቁም ፥ ማኅበረ ተኞች ፡ በሥራ ፡ አስኪያጁ ፡ ሥልጣን ፡ ላይ ፡ ወሰን ፡ ማድረግ ፡ ስለሚችሉ ፡ ነው ።[32] የማኅበሩ ፡ አለመመዝገብ ፡ በሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ ላይ ፡ ምንም ፡ ዓይነት ፡ ውጤት ፡ አያስከትልም ፤ ምክንያቱም ፥ በማስታወቂያ ፡ ያልወጣ ፡ ነገር ፡ በእነርሱ ፡ ላይ ፡ ተፈ ጻሚ ፡ ስለማይሆን ፡ ነው ። በማኅበሩም ፡ መመዝገብ ፡ ሶስተኛ ፡ ወገኖች ፡ የሚያጡት ፡ ነገር ፡ የለም ። ምንም ፡ እንኳን ፡ የንግድ ፡ መዝገቡ ፡ ከማኅበሩ ፡ ጋር ፡ የንግድ ፡ ግን ኙነት ፡ ለማድረግ ፡ ለሚመኙት ፡ ሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ በቂ ፡ መረጃ ፡ ለመስጠት ፡ ቢችል ፥ ባለመመዝገቡ ፡ ማሕበሩን ፡ ሕጋዊ ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ መንፈግ ፡ በቂ ፡ ቅጣት ፡ ሊሆን ፡ የሚችል ፡ አይመስልም ።

የግል ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎችን ፡ ጉዳይ ፡ ስንመለከት ፡ ሁኔታው ፡ የተለየ ፡ ይሆናል። ከዚህ ፡ በላይ ፡ እንደተመለከተው ፡ አንድ ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ሕጋዊ ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ ካለው ፡ ድርጅቱ ፡ ራሱ ፡ የንብረት ፡ ባለቤት ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ። አንድ ፡ ማኅ በረተኛ ፡ የግል ፡ ንብረቱን ፡ ለማኅበሩ ፡ ቢያዋጣ ፡ የተባለው ፡ መዋጮ ፡ የሽርክናው ፡

26. የመመዝገብ ፡ ዘዴ ፡ ምናልባት ፡ ብዙ ፡ ፖሊሲዎች ፡ አሉት ። ለምሳሌም ፡ የሽርክና ፡ ማኅበሮች ፡ (ወይም ማንኛውም ፡ ዓይነት ፡ የሥራ ፡ ማኅበሮች ፡) ተመዝግበው ፡ ሲገኙ ፡ ለቀረጥ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ የሚያስ ፈልገውን ፡ ማስረጃ ፡ ያቀርባሉ ። ያልተመዘገቡ ፡ ማኅበሮች ፡ የገንዘብ ፡ መቀጫ ፡ ይከፍላሉ ። (የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፪፲፭ን ፡ እና ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፩፻፷፰ን ፡ ይመለከቷል) ። እንደዚህም ፡ ያለው ፡ ፖሊሲ ፡ ስለ ፡ ሕጋዊ ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ መከልከል ፡ ማብራሪያ ፡ አይሰጥም ።

27. የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቍ. ፩፻፲፯ ።

28. የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቍ. ፩፻፹፱ ፡ (፩) (የሕጉን ፡ የአማርኛ ፡ ወይም ፡ የፈረንሣይኛ ፡ ቅጂ ፡ ይመለከቷል)።

29. የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቍ. ፩፻፲፯ ፡ (፬) ።

30. የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቍ. ፩፻፹፱ ፡ (፪) ።

31. የሽርክናን ፡ ማኅበር ፡ ስለመመዝገብ ፡ ሕግ ፡ በሌለበት ፡ በዩናይትድ ፡ ስቴትስ ፡ የሥራ ፡ አስኪያጁ ፡ ስል ጣን ፡ መወሰን ፡ በሶስተኛ ፡ ወገን ፡ ላይ ፡ ውጤት ፡ የሚኖረው ፡ ሶስተኛው ፡ ወገን ፡ ስለዚሁ ፡ ወሰን ፡ የሚያውቅ ፡ የሆነ ፡ እንደሆን ፡ ብቻ ፡ ነው ። ማስታወቂያ ፡ እንዲተሰጠ ፡ ምንም ፡ ዓይነት ፡ መንገድ ፡ የለም ። ዩኒፎርም፡ ፓርትነርሺፕ ፡ አክት ፡(ዩ፡ ኤስ ፡ ኤ)፡ ቍ. ፱ (፬) ፥ በጁ ፡ ክሬን ፥ ሃንድ ፡ ቡክ ፡ ኦን ፡ ዘ ፡ ሎው ፡ ኦቭ ፡ ፓርትነርሺፕ ፡ (፪ኛ ፡ እትም ፡ ፲፱፻፶፪) ፡ ውስጥ ፡ ገጽ ፡ ፭፻፶፫ ።

32. ኤ ፡ ኮርቢን ፡ ኤ ፡ ትራቲይስ ፡ ኦን ፡ ዘ ፡ ሩልስ ፡ ኦቭ ፡ ኰንትራክት ፡ ሎው ፡ (፲፱፻፶፩) ፡ ፫ልዩም፡ ፮ ፥

ማኅበር ፡ ንብረት ፡ ይሆናል ። የማኅበረተኛውን ፡ የግል ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ ጉዳይ ፡ ስንመለከት ፡ የዕዳዎቹ ፡ ክፍያ ፡ ሊሆን ፡ ይችል ፡ የነበረው ፡ ገንዘብ ፡ የሌላ ፡ ሰው ፡ ንብረት ፡ ሆኖ ፡ እናገኘዋለን ። አሁን ፡ በተባለው ፡ ገንዘብ ፡ ፈንታ ፡ የአለው ፡ ንብረት ፡ ማኅበረተኛው ፡ በማሕበሩ ፡ ውስጥ ፡ የአለው ፡ ድርሻ ፡ ነው ። ከዚህ ፡ በላይ ፡ እንደ ፡ ተመለከትነው ፡ የግል ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎቹ ፡ በማኅበረተኛው ፡ መብት ፡ ሊጠቀሙ ፡ ቢችሉም ፡ ይህ ፡ መብት ፡ ከማኅበሩ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ መብት ፡ ዝቅተኛ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ የገንዘብ ፡ ጠያቂዎቹን ፡ ጉዳይ ፡ ስንመለከት ፡ ማኅበረተኛው ፡ ንብረቱን ፡ ዝቅተኛ ፡ ዋጋ ፡ በአለው ፡ ነገር ፡ ለውጦታል ፡ ለማለት ፡ እንችላለን ።

ቍ. ፪፻፳፫፡ለግል፡ገንዘብ፡ጠያቂዎች፡ ከዚህ፡ሁኔታ፡የሚጠበቁበትን፡ አንድ፡ መንገድ፡ ይፈጥራል።የተበዳሪው፡ማኅበረተኛ ፡ ንብረት ፡ የማኅበሩ ፡ ንብረት ፡ የሚሆነው ፡ ማኅበሩ፡ የተመዘገበና ፡ በማስታወቂያ ፡ የወጣ ፡ ሲሆን ፡ ብቻ፡ነው ። ይህ ፡ በሚሆንበት፡ጊዜ፡የግል ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ ማኅበሩ ፡ ከመቋቋም ፡ እንዲታገድ ፡ ለማድረግ ፡ አይችሉም ። ነገር ፡ ግን ፡ አስቀድሞ ፡ ከባለዕዳው ፡ ማኅበረተኛ ፡ ድርሻ ፡ ላይ ፡ ገንዘባቸው ፡ እንዲ ከፈላቸው ፡ ለማድረግ ፡ ይችላሉ ። ይህ ፡ ጠቃሚ ፡ የሚሆንበት ፡ ምክንያት ፡ ማኅበሩ ፡ ተቋቁሞ ፡ ሥራ ፡ ከመጀመሩ ፡ በፊት ፡ ማኅበረተኛው ፡ በማኅበሩ ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ ንብረት ፡ እና፡ማኅበሩ ፡ ሳይጀመር ፡ ያዋጣው ፡ ንብረት ፡ ዋጋ ፡ አንድ ፡ በመሆኑ ፡ ነው ። ይህም፡ማኅበሩ፡ሥራ፡ስላልጀመረ፡የባለዕዳው ፡ ማኅበርተኛ ፡ ንብረት፡ሊቀነስ፡አይችልም ፡ ማለት ፡ ነው ። እንዲሁም ፡ ከማኅበሩ ፡ ገንዘብ ፡ የሚጠይቁ ፡ ሰዎች ፡ ስለሌሉ ፡ በአከ ፋፈል ፡ ረገድ ፡ የግል ፡ ባለገንዘቡ ፡ ወደ ፡ መጨረሻ ፡ የሚደረግበት ፡ ምክንያት ፡ የለም ።

ሕጋዊ ፡ ህላዌ ፡ ቍ. ፪፻፳፫ ፡ ላልተመዘገበና ፡ በማስታወቂያ ፡ ላልወጣ ፡ ማኅ በር ፡ በሕግ ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ ከመንፈጉም ፡ በላይ ፡ "መኖሩም ፡ አይታወቅለ ትም" ይላል ። በዚህ ፡ ረገድ ፡ የቍ. ፪፻፳፫ ፡ ትርጉም ፡ ግልጽ ፡ አይደለም ፤ ምክንያ ቱም ፡ ሕጋዊ ፡ ህላዌ ፡ እንደ ፡ ሕጋዊ ፡ ሰውነት ፡ መብት ፡ በአንግሎ - አሜሪካን ፡የሕግ ቅንጅት ፡ ውስጥ ፡ የታወቀና ፡ የማይለወጥ ፡ ትርጉም ፡ ስለሌለው ፡ ነው ። በፈረንሣይ ፡ ሕግም ፡ ሁኔታው ፡ ተመሳሳይ ፡ ነው ። ሕጋዊ ፡ ሕላዌና ፡ በሕግ ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ አንድ ፡ ናቸው ፡ ብሎ ፡ መገመት ፡ በሕግ ፡ አውጪው ፡ በኩል ፡ እንዳልታሰበበት ፡ ስለ ሚያስቆጥር ፡ ምን ፡ ዓይነት ፡ ትርጉም ፡ ሊኖረው ፡ እንደሚችል ፡ መፈለግ፡ተገቢ ፡ ነው።

ማኅበሩ ፡ "መኖሩም ፡ አይታወቅም" ሲባል፡ሕጉ፡ጭራሽ፡በማኅበሩ፡ጉዳይ፡ ውስጥ ፡ መግባት ፡ አያስፈልገውም ፡ ማወቅም ፡ የለበትም ፡ የሚል ፡ ትርጉም ፡ ሊሰጠው ፡ ይችላል ። የዚህ ፡ አስተሳሰብ ፡ ምሳሌ ፡ በአሜሪካን ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ ይገኛል ። አንድ ፡ ማኅበር ፡ የተቋቋመው ፡ እንደ ፡ ቍማርና ፡ እንደ ፡ ዘረፋ ፡ ላሉት ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ ተግባ ሮች ፡ ከሆነ ፡ የአሜሪካን ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ እነዚህን ፡ ድርጅቶች ፡ ፈጽሞ ፡ ባለማወቃ ቸው ፡ በማኅበረተኞች ፡ መካከል ፡ ሂሣብ ፡ እንዲጣራ፡ እንኳን፡ ሳይፈቅዱ፡ ቀርተዋል ።[32] የሚገባውን ፡ የማስታወቂያ ፡ ዘዴ ፡ አለመፈጸም ፡ የዚህን ፡ ዓይነት ፡ ሁኔታ ፡ ያስ ከትላል ፡ ማለት ፡ ቅጣቱን ፡ በጣም ፡ ከፍተኛ ፡ ስለሚያደርግ ፡ ተገቢ ፡ አተረጓጎም ፡ አይመስልም ።

ሌላ ፡ ትርጓሜ ፡ ደግሞ ፡ ማኅበሩ ፡ "መኖሩ ፡ አይታወቅም" ሲባል ፡ ማኅበሩ ፡ ያለው ፡ ሕጋዊ ፡ ባልሆነ ፡ ሁኔታ ፡ ነው ፡ ሊባል ፡ ይቻላል ። ይህ ፡ የታወቀ ፡ ስለሆነ ፡ መደጋገም ፡ አያስፈልግም ፤ ስለዚህ ፡ እስካሁን ፡ ድረስ ፡ የተሰጡት ፡ ትርጓሜዎች ፡ አጥጋቢ ፡ አይደሉም ፡ ማለት ፡ ነው ።

ሌላው ፡ ትርጓሜ ፡ ደግሞ ፡ የማኅበሩ ፡ ሕጋዊ ፡ ህላዌ ፡ ማጣት ፡ የማኅበር ፡ ውሉን፡ የማይጸና ፡ ያደርገዋል ፡ የሚል ፡ ነው ። ይህ ፡ አተረጓጎም ፡ ሕጋዊ ፡ ሕላዌ ፡ የተባለውን ፡

ከሕጋዊ ፡ ሰውነት ፡ የመለየት ፡ ጥቅም ፡ አለው ። የዚህ ፡ ዓይነቱ ፡ ደንብ ፡ አስደናቂ ፡ ሆኖ ፡ መታየት ፡ የለበትም ፤ ምክንያቱም ፡ እንደ ፡ ፈረንሣይና[33] ፡ እንደ ፡ ሌባኖን ፡[34] ባሉት ፡ አገሮች ፡ አለማስመዝገብ ፡ ስምምነቱን ፡ ፈራሽ ፡ ስለሚያደርገው ፡ ነው ። የውሉ ፡ አለመጽናት ፡ የመጀመሪያና ፡ ዋናው ፡ ውጤት ፡ ውሉን ፡ የማይፈጸም ፡ ማድረጉ ፡ ነው። ከዚህ ፡ በታች ፡ እንደምናየው ፡ የስምምነት ፡ አለመጽናት ፡ ከሕጋዊ ፡ ሰውነት ፡ መነፈግ ፡ የከበደ ፡ "ቅጣት" ነው ።

ይህ ፡ እንዳይሆን ፡ የሚያደርጉ ፡ ሁለት ፡ ክርክሮች ፡ አሉ ። በመጀመሪያ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ "ተቃራኒ ፡ ድንጋጌ ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ ስለ ፡ ውል ፡ ጉዳይ ፡ የተወሰኑ ፡ የማስታወቂያ ፡ ድንጋጌዎች ፡ አለመፈጸም ፡ ውሉን ፡ ፈራሽ ፡ አያደርገውም፡"[35] ይላል ። ይህ ፡ ሕግ ፡ ተፈጻሚ ፡ በማይሆንበት ፡ ጊዜ ፡ ሕጉ ፡ ተመሳሳይ ፡ በሆነ ፡ ግልጽ፡ ቋንቋ ፡ መደንገግ ፡ አለበት ። "መኖሩ ፡ አይታወቅም" የሚሉት ፡ ቃላት ፡ ግልጽ ፡ ስላልሆኑና ፡ ሕግ ፡ አውጪው ፡ ክፍል ፡ ውጤቱ ፡ ይህ ፡ እንዲሆን ፡ ከፈቀደ ፡ በግልጽ ፡ ቋንቋ ፡ "ፈራሽ" ይሆናል ፡ ብሎ ፡ ለመደንገግ ፡ ይችል ፡ ስለነበር ፡ ይህ ፡ ክርክር ፡ ደካማ ፡ ይሆናል ።

ሁለተኛ ፡ ደግሞ ፡ ቍ. ፪፻፲፬ ፡ ግልጽ ፡ በሆነ ፡ ቋንቋ ፡ በጽሑፍ ፡ ያልተደረገ ፡ የማኅበር ፡ መቋቋሚያ ፡ ስምምነት ፡ አይጸናም ፡ ይላል ። ሕግ ፡ አውጪው ፡ አለማስመዝገብም ፡ ተመሳሳይ ፡ ውጤት ፡ እንዲኖረው ፡ ፈልጎ ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ በተመሳሳይ ፡ ቋንቋ ፡ ይጠቀም ፡ ነበር ። ቍ. ፪፻፴፫ን ፡ ውሉን ፡ እንደማይጸና ፡ እንደሚያደርገው፡ አድርጎ ፡ መተርጎም ፡ ነገሩን ፡ መደጋገም ፡ ይሆናል ። ያልተጻፈ ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ውል ፡ ሊመዘገብ ፡ አይችልም ። ቍ. ፪፻፳፫ ፡ ውሎች ፡ እንዳይጸኑ ፡ የሚያደርግ ፡ ቢሆን ኖሮ ፡ ስላልተጻፉ ፡ ስምምነቶች ፡ ሌላ ፡ ቍጥር ፡ አስፈላጊ ፡ አይሆንም ፡ ነበር ።

ስለዚህ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተገለጸው ፡ መሠረት ፡ ሕግ ፡ አውጪው ፡ ማኅበሩ ፡ "መኖሩም"አይታወቅም ሲል ፡ ያልተመዘገቡ ፡ ማኅበሮች ፡ ከማኅበረተኞቹ ፡ የተለየ ፡ ሰውነት ፡ የላቸውም ፡ የሚለውን ፡ በአንክሮ ፡ ለመግለጽ ፡ አስቦ ፡ ነው ፡ ማለት ፡ ያስፈልጋል ።

<u>የሕጋዊ ፡ ሰውነት ፡ መብት ፡ እጦት ፡ በሌሎች ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ሕግ ፡ ክፍሎች ፡ ላይ ፡ የሚያስከትለው ፡ ውጤት ።</u>

ከላይ ፡ እንደተጠቀሰው ፡ የሕጋዊ ፡ ሰውነት ፡ መብት ፡ መነፈግ ፡ ዋና ፡ ትርጉሙ፡ የሚታወቀው ፡ ማኅበሩ ፡ ፈርሶ ፡ ንብረቱ ፡ ለገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ በሚከፋፈልበት ፡ ጊዜ ፡ ነው ። ማኅበሩ ፡ በሚሠራበትም ፡ ጊዜ ፡ የሕጋዊ ፡ ሰውነት ፡ ጉዳይ ፡ አስፈላጊ ፡ የሚሆንባቸው ፡ አንዳንድ ፡ ጥያቄዎች ፡ ሊነሱ ፡ ይችላሉ ። እነዚህም ፡ ስለ ፡ መዋጮ ፡ ጉዳይ ፡ ስለ ፡ ሥራ ፡ አስኪያጆች ፡ ሥልጣንና ፡ ስለ ፡ አላፊነት ፡ መወሰን ፡ ናቸው ።

---

33. የጁላይ ፡ ፳፬ ፡ ፲፰፻፷፯ ፡ ሕግ ፡ (የፈረንሣይ) ፡ በዴክር ፡ ኤል ፡ ፴ ፡ ኦክቶበር ፡ ፲፱፻፴፭ ፡ ቍ ፶፰ ፡ በኮድ ፡ ደ ፡ ኮሜርስ ፡ (ፔቲ ፡ ኮድ ፡ ዳሎዝ ፡ ፶፰ኛ ፡ እትም ፡ ፲፱፻፷፪)፡ ውስጥ ፡ ገጽ ፡ ፶፪ ፡ እንደተሻሻለ ። በመጀመሪያ ፡ የንግድ ፡ ልምድ ፡ ተከትሏል ፡ ብሎ ፡ ለመከራከር ፡ ይቻል ፡ ይሆናል ። ይሁን ፡ እንጂ፡ በፈረንሣይ ፡ አገር ፡ የደረሱትን ፡ ችግሮች ፡ ለማስወገድ ፡ ቍጥር ፡ ፪፻፴፫ን ፡ ፕሮፌሰር ፡ ኤስካራ ፡ ከሞቱ ፡ በኋላ ፡ በሕጉ ፡ ረቂቅ ፡ ውስጥ ፡ ያስገቡት ፡ ፕሮፌሰር ፡ ጂዮፍሬ ፡ ነበሩ ።

34. ኮድ ፡ ደ ፡ ኮሜርስ ፡ (ሊባኖስ) ፡ ቍ. ፵፬ ፡ ኢ. ቦስታኒ ፡ ኮድ ፡ ሊባኒስ ፡ ኤን ፡ ቴክስት ፡ ፍራንሴ ፡ (፲፱፻፶፫) ። ይህን ፡ የሚያቀርበውን ፡ ሳይመዘግቡ ፡ የቀሩትን ፡ የንግድ ፡ ድርጅቶች ፡ በሕግ ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ በመከልከል ፡ የሚቀጣውን ፡ የታይላንድን ፡ የፍትሐ ፡ ብሔርና ፡ የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቍ ፩ሺ፲፭ ፡ (፲፱፻፷፪) ፡ ይመለከቷል ።

35. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍ. ፩ሺ፯፻፹ ፡ (፫)

መዋጮዎች ፡— ማኅበሩ ፡ ሕጋዊ ፡ ሰውነት ፡ ሲኖረው ፡ በራሱ ፡ ስም ፡ የንብረት ፡ ባለቤት ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ። ከማኅበሩ ፡ ንብረቶች ፡ መካከል ፡ አንዱ ፡ ማኅበረተኞች ፡ የሚያደርጉት ፡ መዋጮ ፡ ነው ፤ ማኅበረተኞቹ ፡ የመዋጮአቸው ፡ ባለቤቶች ፡ ሆነው ፡ አይቆዩም ፤ ባለቤትነቱ ፡ ያልተከፋፈለ ፡ የጥቅም ፡ ማግኛ ፡ መብት ፡ በማሕበሩ ፡ ላይ ፡ ይኖራቸዋል ፤ ማኅበሩ ፡ ሕጋዊ ፡ ሰውነት ፡ ባልተሰጠው ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ ራሱ ፡ የንብረት ፡ ባለቤት ፡ ሊሆን ፡ አይችልም ። እዚህ ፡ ላይ ፡ የሚነሣው ፡ ጥያቄ ፡ እያንዳንዱ ፡ ማኅበረተኛ ፡ የራሱ ፡ ንብረት ፡ ባለቤት ፡ ይሆናል ፡ ወይስ ፡ ማኅበረተኞቹ ፡ በጠቅላላው ፡ ላዋጡት ፡ ንብረት ፡ የጋራ ፡ ባለቤቶች ፡ ይሆናሉ ፡ የሚል ፡ ነው ።[36] ለዚህ ፡ ጥያቄ ፡ መልስ ፡ ለማግኘት ፡ አስቀድመን ፡ መገንዘብ ፡ ያለብን ፡ የሽርክናው ፡ ማሕበር ፡ ውል ፡ በወገኖቹ ፡ መካከል ፡ የሚጸና ፡ መሆኑን ፡ ነው ። ስምምነታቸው ፡ በጽሑፍ ፡ በሆነበት ፡ ጊዜ ፡ ውሉ ፡ ባይመዘገብም ፡ የሚጸና ፡ መሆኑን ፡ አይተናል ። ማኅበሩ ፡ የሕጋዊ ፡ ሰውነት ፡ መብት ፡ ባልተሰጠው ፡ ጊዜ ፡ ማኅበረተኞቹ ፡ የንብረቱ ፡ የጋራ ፡ ባለቤቶች ፡ ይሆናሉ ። ይህን ፡ መፍትሔ ፡ እያንዳንዱን ፡ ማኅበረተኛ ፡ የራሱ ፡ ንብረት ፡ ባለቤት ፡ ከማድረግ ፡ የተሻለና ፡ በርትዕ ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ የሚያደርጉት ፡ ሁለት ፡ ነጥቦች ፡ አሉ ።

በመጀመሪያ ፡ ይህ ፡ መፍትሔ ፡ የተዋዋዮቹን ፡ ፍላጎት ፡ የሚያረካ ፡ ይሆናል ። በአንድ ፡ የተለመደ ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ውል ፡ መሠረት ፡ ማኅበረተኞቹ ፡ በተለይ ፡ የተሰየሙ ፡ የንብረት ፡ ዓይነቶችን ፡ ለማዋጣት ፡ ቢችሉም ፡ ያዋጡት ፡ ንብረት ፡ እንዲመለስላቸው ፡ ለመጠየቅ ፡ አይችሉም ። አንድ ፡ ማኅበረተኛ ፡ ሊጠይቅ ፡ የሚችለው የመዋጮውን ፡ ዋጋ ፡ ብቻ ፡ ነው ።[37] ማኅበሩን ፡ ኪሣራ ፡ ካጋጠመው ፡ በኪሣራው ፡ ማኅበረተኞቹ ፡[38] በሙሉ ፡ ተካፋዮች ፡ መሆን ፡ አለባቸው ፡ እንጂ ፡ መዋጮአቸው ፡ በኪሣራው ፡ ምክንያት ፡ የጠፋባቸው ፡ ብቻ ፡ መካፈል ፡ የለባቸውም ። እያንዳንዱ ፡ ማኅበረተኛ ፡ የመዋጮው ፡ ባለቤት ፡ ሆኖ ፡ ይኑር ፡ ማለት ፡ ይህን ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር፡ ውል ፡ ዋና ፡ መሠረተ ፡ አሳብ ፡ የሚያፋልስ ፡ ይሆናል ። በዚህም ፡ የሚጎዱት ፡ እንደ ፡ ገንዘብ ፡ ያሉትን ፡ የሚያልቁ ፡ ነገሮች ፡ ያዋጡ ፡ ማኅበረተኞች ፡ ናቸው ። ለምሳሌ ፡ ሀ ፡ ለና ፡ ሐ ፡ በጽሑፍ ፡ ማኅበር ፡ ለማቋቋም ፡ ይስማማሉ ፤ ስምምነታቸውን ፡ ግን ፡ አያስመዘግቡም ፤ ሀና ፡ ለ ፡ እያንዳንዳቸው ፡ አምስት ፡ ሺ ፡ ብር ፡ ሲያዋጡ ፡ ሐ ፡ ደግሞ ፡ አምስት ፡ ሺ ፡ ብር ፡ የሚያወጣ ፡ መሣሪያ ፡ ያዋጣል ። ከጊዜ ፡ በኋላ ፡ የንግድ ፡ ድርጅቱ ፡ ያለው ፡ ንብረት ፡ መሣሪያውና ፡ ሦስት ፡ ሺ ፡ ብር ፡ በጥሬ ፡ ገንዘብ ፡ ይሆናል ። በኪሣራው ፡ ምክንያት ፡ ሐ ፡ መዋጮውን ፡ መልሶ ፡ ለመውሰድ ፡ መብት ፡ ካለው ፡ ሀና ፡ ለ ፡ ብቻ ፡ ሰባት ፡ ሺ ፡ ብር ፡ የሆነውን ፡ ኪሣራ ፡ ይችላሉ ፡ ማለት ፡ ነው ። ይህ ፡ ማኅበረተኞች ፡ ያልፈለጉት ፡ ውጤት ፡ መሆኑ ፡ ግልጽ ፡ ነው ።

ሁለተኛ ፡ ማኅበረተኞቹ ፡ የመዋጮዋቸው ፡ የግል ፡ ባለቤቶች ፡ ሆነው ፡ ይኖራሉ ፡ ማለት ፡ አንዳንድ ፡ የግል ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎችን ፡ ብቻ ፡ የመጠበቅና ፡ ሌሎችን ፡ የአለመጠበቅ ፡ ውጤት ፡ ያስከትላል ። ወደ ፡ ምሳሌያችን ፡ እንመለስና ፡ ማኅበሩ ፡ ከመቋቋሙ ፡ በፊት ፡ ለ ፡ ከመ ፡ ላይ ፡ አምስት ፡ ሺ ፡ ብር ፡ ሲበደር ፡ ሐም ፡ ከሠ ፡ ላይ ፡ አምስት ፡ ሺ ፡ ብር ፡ ተበድሯል ፡ እንበል ። ሀ ፡ እና ፡ ለ ፡ ሌላ ፡ ንብረት ፡ የላቸውም ። ከዚህ ፡ በላይ ፡ እንደተጠቀሰው ፡ ኪሣራ ፡ ይፈጠራል ። ሠ ፡ ከሐ ፡ ላይ ፡

---

36. ከመዋጮዎቹ ፡ ዋጋ ፡ በላይ ፡ የሆኑት ፡ ንብረቶች ፡ እንደ ፡ ትርፍ ፡ ይቆጠራሉ ። በማኅበረተኞቹ ፡ ስም ፡ የተገኙ ፡ ስለሆኑም ፡ የማኅበረተኞቹ ፡ የጋራ ፡ ንብረቶች ፡ መሆን ፡ አለባቸው ።

37. የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቍ. ፪፻፷፱ ።

38. የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቍ. ፪፻፸ ፡ (፪) ።

አምስት ፡ ሺ ፡ ብሩን ፡ ለማግኘት ፡ ይችላል ፤ ምክንያቱም ፤ የሐ ፡ ንብረት ፡ ስለሚመልስለት ፡ ነው ። መ ፡ ግን ፡ ለማግኘት ፡ የሚችለው ፡ አንድ ፡ ሺ ፡ ብር ፡ ብቻ ፡ ይሆናል ፤ ምክንያቱም ፡ ከቀረው ፡ ሶስት ፡ ሺ ፡ ብር ፡ ለና ፡ ሐ ፡ ተካፋዮች ፡ ስለሚሆኑ ፡ ነው ። መ ፡ እና ፡ ሠ ፡ ሁለቱም ፡ ቅን ፡ ልቡና ፡ የአላቸው ፡ ሶስተኛ ፡ ወገኖች ፡ ቢሆኑም ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ ውጤት ፡ አላጋጠማቸውም ፡ ማለት ፡ ነው ።

<u>የሥራ ፡ አስኪያጅ ፡ ሥልጣን</u> ፡— የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ሥራ ፡ አስኪያጅ ፡ ሥልጣን ፡ ማናቸውንም ፡ የሽርክናውን ፡ ማኅበር ፡ ዓላማ ፡ የማይቃወሙ ፡ ግዴታዎችን ፡ ለመፈጸም ፡ የሚያስችል ፡ ነው ።[39] የዚህ ፡ ሥልጣን ፡ ወሰን ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ መሠረት ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ሥራ ፡ አስኪያጅ ፡ ሲባል ፡ ካለው ፡ ሥልጣን ፡ በጣም ፡ የበለጠ ፡ ነው ። ምክንያቱም ፡ ይህ ፡ መሾም ፡ እንደ ፡ አንድ ፡ "በጠቅላላ ፡ አነጋገር ፡ የተደረገ" የሥልጣን ፡ አሰጣጥ ፡ ሆኖ ፡ ስለሚቆጠር ፡ ነው ። አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ይህ ፡ ሥልጣን ፡ "የአስተዳደር ፡ ሥራን" ብቻ ፡ ለማከናወን ፡ የሚያስችል ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ ይተረጐማል ።[40] አንድ ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ያልተመዘገበ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የ"ሥራ ፡ አስኪያጁ" ወኪልነት ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ እንጂ ፡ በንግድ ፡ ሕግ ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ አይደለም ፡ ማለት ፡ ነውን ? ይህ ፡ ከሆነ ፡ አንድ ፡ ሶስተኛ ፡ ወገን ፡ ሰፊ ፡ ሥልጣን ፡ የአለው ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ሥራ ፡ አስኪያጅ ፡ ነው ፡ በማለት ፡ ከአንድ ፡ ወኪል ፡ ጋር ፡ ከተዋዋለ ፡ ይህን ፡ ወኪል ፡ ከሥልጣኑ ፡ ወሰን ፡ ወጥቶ ፡ የተዋዋለ ፡ ወኪል ፡ ሆኖ ፡ ሊያገኘው ፡ ይችላል ። በእንደዚህ ፡ ያለ ፡ ጊዜ ፡ "የሽርክናው ፡ ማኅበር" ፡ በውሉ ፡ አይገደድም ።

ማኅበርተኞቹ ፡ ወኪላቸው ፡ ማለት ፡ ሥራ ፡ አስኪያጁ ፡ የአንድ ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ሥራ ፡ አስኪያጅ ፡ ሥልጣን ፡ እንዲኖረው ፡ ከፈለጉ ፡ ምንም ፡ ዓይነት ፡ ችግር ፡ አይገጥመንም ። ይህን ፡ ጉዳይ ፡ የሚመለከቱት ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ደንቦች ፡ ለአተረጓጐም ፡ ብቻ ፡ የሚረዱ ፡ ደንቦች ፡ ናቸው ። የወኪሉ ፡ የሥልጣን ፡ ወሰን፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ የሚረጋግጠው ፡ ሁለቱም ፡ ወገኖች ፡ በነበራቸው ፡ ፈቃድ ፡ መሠረት ፡ ነው ።[41] ችግር ፡ ሊገጥመን ፡ የሚችለው ፡ ተዋዋዮቹ ፡ የሥራ ፡ አስኪያጁን ፡ ሥልጣን ፡ ወሰን ፡ ለማጥበብ ፡ ፈቃድ ፡ ከነበራቸው ፡ ነው ። በንግድ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ የሥራ ፡ አስኪያጁ ፡ ሥልጣን ፡ የሚወሰነው ፡ "የውል ፡ ቃሎች ፡ ሶስተኛ ፡ ወገኖችን ፡ መቃወሚያ ፡ የሚሆኑበት ፡ በንግድ ፡ መዝገብ ፡ የተመዘገቡ ፡ እንደሆነ ፡ ወይም፡ ሶስተኛ ፡ ወገኖች ፡ አኳኋኑን ፡ የሚያውቁ ፡ መሆናቸው ፡ የተረጋገጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው" ፡[42] ይህ ፡ ድንጋጌ ፡ የንግድ ፡ ሁኔታ ፡ የተረጋገጠ ፡ እንዲሆን ፡ የሚረዳ ፡ እንደ መሆኑ ፡ መጠን ፡ መከበር ፡ አለበት ። የሽርክና ፡ ማኅበሩ ፡ ስለአልተመዘገበ ፡ የሥራ ፡ አስኪያጁን ፡ ሥልጣን ፡ የሚያጠቡት ፡ ወሰኖች ፡ እንደ ፡ መቃወሚያ ፡ የሚያገለግሉት ፡ አኳኋኑን ፡ ማወቃቸው ፡ በተረጋገጠባቸው ፡ ሶስተኛ ፡ ወገኖች ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ መሆን ፡ አለበት ።

<u>የተወሰነ ፡ አላፊነት</u> ፡— ሁለት ፡ ዓይነት ፡ አላፊነት ፡ ያለበት ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ተቋቁሞ ፡ በአለመመዝገቡ ፡ የሚደርሰው ፡ ሕጋዊ ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ እጦት ፡ የሁሉንም ፡ ማኅበርተኞች ፡ አላፊነት ፡ ያልተወሰነ ፡ ያደርገዋል ፡ ወይ ፡ የሚለው ፡ ጥያቄ ፡ ይነሳል ።

---

39. የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቍ ፪፻፹፱ ፡ (፩) ፡ (የፈረንሣይኛውን ፡ ቅጂ ፡ ይመለከቷል ) ።
40. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍ. ፡ ፪ሺ፪፻፫ ።
41. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍ. ፪ሺ፩፻፹፮ ፡ (፩) ።
42. የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቍ. ፪፻፹፱ ፡ (፪) ።

ሁለት ፡ ዓይነት ፡ አላፊነት ፡ ያለበት ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ የሁሉም ፡ ሳይሆን ፡ የአንዳንዶቹ ፡ ማኅበረተኞች ፡ አላፊነት ፡ የተወሰነ ፡ የሚሆንበት ፡ ድርጅት ፡ ነው ።[43] የተወሰነ ፡ አላፊነት ፡ ያላቸው ፡ ማኅበረተኞች ፡ መኖራቸው ፡ እንደ ፡ እሽሙር ፡ ማኅበር ፡ የተካፋዮች፡ ስም ፡ ሳይደበቅ ፡ ለሶስተኛ ፡ ወገኖች ፡ ይገለጻል ። ስማቸውም ፡ በተመዘገበው ፡ የማኅበሩ ፡ መመሥረቻ ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ ይዘረዘራል ።[44] በሶስተኛ ፡ ወገኖች ፡ ዘንድ ፡ ያልተወሰነ ፡ አላፊነት ፡ እንዳላቸው ፡ አድርጐ ፡ ሊያሳስት ፡ የሚችል ፡ አድራጎት ፡ ካላሳዩ ፡ በስተቀር ፡ የተወሰነ ፡ አላፊነት ፡ ያላቸው ፡ ማኅበረተኞች ፡ አላፊነታቸው ፡ ለማኅበሩ ፡ ግዴታዎች ፡ ብቻ ፡ እንዲሆን ፡ አድርገው ፡ እንዲወስኑ ፡ ሕጉ፡ ይፈቅድላቸዋል ። የተወሰነ ፡ አላፊነት ፡ ያለው ፡ ማኅበረተኛ ፡ በሽርክናው ፡ ማኅበር፡ ሥራ ፡ አካሄድ ፡ ቢገባ ፡ በአሠራሩ ፡ ለደረሱት ፡ ግዴታዎች ፡ ከማኅበሩ ፡ ጋር ፡ ባንድነትና ፡ ሳይከፋፈል ፡ ያለወሰን ፡ አላፊ ፡ ይሆናል ።[45]

ይህ ፡ ድንጋጌ ፡ በግልጽ ፡ ከሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ጋራ ፡ የሚዋዋሉ ፡ የሶስተኛ ፡ ወገኖችን ፡ መብት ፡ (ጥቅም) አብልጦ ፡ የሚጠብቅ ፡ ነው ። በሌላ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ በተወሰነ ፡ አላፊነትና ፡ በሕግ ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ ስለ ፡ መኖር ፡ መካከል ፡ ግንኙነት ፡ መኖሩ ፡ ግልጽ ፡ አይደለም ። ምንም ፡ እንኳን ፡ የእሽሙር ፡ ማኅበር ፡ በሕግ ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ ባይሰጠው ፡[46] እና ፡ የተመዘገበ ፡ ባይሆንም ፡[47] ስለ ፡ እውነተኛው ፡ አላፊነታቸው ፡ ሶስተኛ ፡ ወገኖች ፡ እንዲሳሳቱ ፡ ካልተደረጉ ፡ በቀር ፡[48] ጥቂቶቹ ፡ ማኅበረተኞች ፡ የተወሰነ ፡ አላፊነት ፡ ሊኖራቸው ፡ ይችላል ።[49] የሶስተኛ ፡ ወገኖችን ፡ መብት ፡ የመጠበቅ ፡ ዓላማ ፡ ከተከበረ ፡ በአልተመዘገበ ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ የሚገኙት ፡ ማኅበርተኞች ፡ የተወሰነ ፡ አላፊነት ፡ ብቻ ፡ እንዲኖራቸው ፡ የማይደረግበት ፡ ምክንያት ፡ የለም ። በአንድ ፡ ጉዳይ ፡ ሶስተኛ ፡ ወገኖች ፡ እንዲሳሳቱ ፡ ተደርገዋል ፡ ለማለት ፡ የሚቻለው ፡ የጉዳዩን ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ በማየት ፡ ነው ። ሆኖም ፡ የሽርክናው ፡ ማኅበር ፡ የአልተመዘገበ ፡ ከሆነ ፡ ሶስተኛ ፡ ወገኖች ፡ በይበልጥ ፡ ሊሳሳቱ ፡ መቻላቸውን ፡ መካድ ፡ ያዳግታል ። የተወሰነ ፡ አላፊነት ፡ ያለው ፡ ማኅበረተኛ ፡ ከሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ ጋራ ፡ የሚያደርጋቸው ፡ ሁሉም ፡ ባይሆኑ ፡ አብዛኛዎቹ ፡ ግንኙነቶች ፡ ያልተወሰነ ፡ አላፊነትን ፡ ያስከትሉበታል ።

## አለመመዝገብና ፡ በማስታወቂያ ፡ አለመግለጽ ፡ ለሽርክና ፡ ማኅበር ፡ መፍረስ ፡ "ትክክለኞች ፡ ምክንያቶች" ፡ ስለ ፡ መሆናቸው ።

ከዚህ ፡ በላይ ፡ እንደተመለከትነው ፡ የአልተመዘገቡ ፡ የሽርክና ፡ ማኅበሮችን ፡ የሚመለከቱት ፡ ችግሮች ፡ የሚነሱት ፡ ማኅበሩ ፡ በሚፈርስበትና ፡ ሒሳብ ፡ በሚጣራበት ፡ ጊዜ ፡ ነው ። በተጨማሪም ፡ አለመመዝገብም ፡ ብቻውን ፡ ለሽርክና ፡ ማኅበር ፡ መፍረስ ፡ ምክንያት ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ። በንግድ ፡ ሕጉ ፡ መሠረት ፡ "ትክክለኞች ፡

43. የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቍ. ፪፻፺፯ ።
44. የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቍ. ፪፻፷፩ ፡ (፩) ።
45. የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቍ. ፪፻፺፰ ።
46. የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቍ. ፫፻፩ ፡ (፫) ። "እንደ፡ ሥራዎቹ ፡ ብዛት ፡ ወይንም ፡ ከባድነት ፡ በተለይ ፡ ለማኅበሩ፡ ግዴታዎች ፡ ሁሉ ፡ ወይንም ፡ ለአንዳንድ ፡ ግዴታ ፡ ብቻ ፡ ሳይከፈል ፡ አላፊ ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ ለመወሰን ፡ ይቻላል ።"
47. የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቍ. ፪፻፷፪ (፫) ።
48. የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቍ. ፪፻፷፪ (፪) ።
49. የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቍ. ፪፻፷፯ ፡ (፪) ።

ምክንያቶች ፡ ኖረውት ፡ ከማኅበርተኞቹ ፡ አንዱ ፡ ባቀረበው ፡ ጥያቄ ፡ ማኅበሩ ፡”
ሊፈርስ ፡ ይችላል ።[50] ከሕግ ፡ ውጭ ፡ በሆነው ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ውስጥ ፡ ማኅበረ
ተኛ፡የሆነ ፡ ሰው ፡ ከሁኔታው ፡ ለመውጣት ፡ ፍላጐት ፡ ይኖረዋል ። ይኸንንም ፡ ለማ
ድረግ ፡ ከሚያስችሉት ፡ መንገዶች ፡ አንዱ ፡ ማኅበሩን ፡ ማፍረስ ፡ ነው ።

ማኅበረተኛው ፡ ማኅበሩን ፡ ለማፍረስ ፡ “ትክክለኞች ፡ ምክንያቶች” አሉት ፡
ማለት ፡ የሽርክናው ፡ ማኅበር ፡ ውል ፡ ሊፈርስ ፡ ይችላል ፡ ማለት ፡ አይደለም ። ከዚህ ፡
በላይ ፡ እንደተጠቀሰው ፡ ውሉ ፡ (በጽሑፍ ፡ ከሆነ) የሚጸና ፡ ነው ። የሚፈርሰው ፡ ድር
ጅቱ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ከመጀመሪያ ፡ ጀምሮ ፡ ውሉ ፡ ዋጋ ፡ እንደሌለው ፡ ቢቆጠር ፡ ኖሮ ፡
ያለፈውን ፡ ሁኔታ ፡ ይነካ ፡ ነበር ፡ ነገር ፡ ግን ፡ የማኅበሩ ፡ መፍረስ ፡ ያለፈውን ፡ ሁኔታ
አለመንካቱ ፡ ማጠራጠር ፡ የለበትም ። ከዚህ ፡ በታች ፡ እንደምንመለከተው ፡ በሕግ ፡
የማይጸና ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ውልን ፡ ማንኛውም ፡ ጥቅም ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ በዚሁ ፡
መሠረት ፡ሊቃወም ፡ ሲችል ፡ “በትክክለኞች ፡ ምክንያቶች” መሠረት ፡ የሽርክና ፡
ማኅበሩ ፡ እንዲፈርስ ፡ ጥያቄ ፡ ለማቅረብ ፡ የሚችለው ፡ ማኅበረተኛው ፡ ብቻ ፡ ነው ።

አንድ ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ በማስታወቂያ ፡ በአለመገለጹ ፡ ተቃዋሚ ፡ ቢነሳ
በት ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ ክሱ ፡ ቢጀመር ፡ የፈረንሳይ ፡ ሕግ ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ውሉ
ተመዝግቦና ፡ በማስታወቂያ ፡ ተገልጾ ፡ ጉድለት፡እንዲታረም ፡ ይፈቅዳል ።[51] ይህም ፡ በኢ
ትዮጵያ ፡ መፈቀድ፡አለበት ። የዚህ ፡ ዓይነቱ ፡ ጉድለት ፡ ትንሽ፡ በመሆኑ ፡ በቀላሉ ፡ ሊታ
ረም ፡ ይችላል ። ይህም ፡ ሆኖ ፡ ምዝገባው ፡ ያለፈውን ፡ ሁኔታ ፡ እንደማይነካ ፡ ግልጽ ፡
ነው ። የሽርክናው ፡ ማኅበር ፡ በሕግ ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ የሚያገኘው ፡ ከተመዘገበ
በት ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ ነው ።[52] ማኅበሩ ፡ ከመመዝገቡ ፡ እና ፡ በማስታወቂያ ፡ ከመገለጹ፡
በፊት ፡ ከማኅበሩ ፡ ላይ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ ወይም ፡ የማኅበረተኞች ፡ የግል ፡ ገን
ዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ የነበሩ ፡ ሶስተኛ ፡ ወገኖች ፡ በንግድ ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፪፻፳፫ ፡ መሠ
ረት ፡ በሚገባ ፡ አኳኋን ፡ የተጠበቁ ፡ ናቸው ። ስለዚህ ፡ ማኅበሩን ፡ መመዝገብና ፡ በማ
ስታወቂያ ፡ መግለጽ ፡ የሚረዳው ፡ ማኅበሩ ፡ እንዳይፈርስና ፡ ለወደፊቱ ፡ በሕግ ፡ የሰ
ውነት ፡ መብት ፡ እንዲያገኝ ፡ ለማድረግ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

<u>ቍጥር ፡ ፪፻፲፬ ፡— “ከእሽሙር ፡ ማኅበር ፡ በተቀር ፡ ማንኛውም ፡ የንግድ ፡
ማኅበር ፡ የሚቋቋምበት ፡ ውል ፡ በጽሑፍ ፡ ካልተደረገ ፡ በቀር ፡ አይጸናም ።”</u>

<u>ስለ ፡ ሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ውል ፡ መፍረስ ፡—</u> እስከ ፡ አሁን ፡ ድረስ ፡ ስንነጋገር
ባቸው ፡ የቆየነው ፡ የአልተመዘገቡ ፡ ግን ፡ በጽሑፍ ፡ የተደረጉ ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡
ውሎች ፡ ናቸው ። በጽሑፍ ፡ ወዳልሆኑት ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ውሎች ፡ ስናልፍ ፡
እነዚህ ፡ ውሎች ፡ ያልተጻፉ ፡ በመሆናቸው ፡ የግድ ፡ ያልተመዘገቡ ፡ መሆናቸውን ፡
ማስታወስ ፡ አለብን ።[53] ውሉ ፡ በጽሑፍ ፡ ባለመሆኑ ፡ ከሚሰጡት ፡ ቅጣቶች ፡ ሌላ ፡
የሽርክናው ፡ ማኅበር ፡ በተጨማሪ ፡ በሕግ ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ አይሰጠውም ።

50. የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቍ. ፪፻፳፪ ፡ (፩) ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ የእሽሙር ፡ ማኅበር ፡ መኖሩን ፡ መግለጽ ፡ ባለዕዳ ፡ የሆኑ ፡ ሶስተኛ ፡ ወገኖች ፡ ማኅበርተኝነታቸው ፡ በተገለጸው ፡ አባሎች፡ ብቻ ፡ ስለእዳው ፡ መክፈል ፡ እን ዲተማመኑ ፡ ሊያደርጋቸው ፡ ይችላል ።
51. የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቍ. ፪፻፲፰ ፡ (፩) ።
52. ሪፔር ፡ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍ. ፳ ፡ የተጠቀሰውን ፡ ገጽ ፡ ፩፻፴፩ ፡ ይመለከቷል ።
53. በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ የተጻፉትን ፡ ድንጋጌዎች ፡ ሲተላለፉ ፡ (የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቍ. ፪፲፭ን ፡ ይመለከቷል) ። ሕጉ ፡ ያለፈውን ፡ ሁኔታ ፡ በመንካት ፡ ከቅጣት ፡ ሊያድን ፡ አይችልም ።

የሽርክናው ፡ ማኅበር ፡ ውል ፡ በጽሑፍ ፡ አለመሆኑ ፡ ስምምነቱን ፡ ራሱን ፡ የማይጸና ፡ ያደርገዋል ።[54] ይህም ፡ ውሉ ፡ በፍጹም ፡ የለም ፡ ወይም ፡ "ከመቅጽበት" ይፈርሳል ፡ ማለት ፡ አይደለም ። ውሉ ፡ አይጸናም ፡ ስንል ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ፍርድ ፡ ቤት፡ ሄዶ ፡ ውሉ ፡ እንዲፈርስ ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል፡ ማለታችን ፡ ነው ። ሁኔታው ፡ በፈቀደው ፡ መሠረት ፡ ይህን ፡ ጥያቄ፡የሚያቀርበው ፡ ተዋዋዮቹ ፡ በአንድነት ፡ ወይም ፡ ከተዋዋዮቹ ፡ አንዱ ፡ ወይም ፡ "ማንኛውም ፡ ጥቅም ፡ ያለው ፡ ሰው ፡" ሊሆን ፡ ይችላል ።[55]

ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ውሉ ፡ እንዲፈርስ ፡ ውሳኔ ፡ ካልሰጠ ፡ ውሉ ፡ እንደጸና ፡ ይቆያል ። ምናልባትም ፡ የማይጸናው ፡ ውል ፡ በሚመለከታቸው ፡ ሰዎች ፡ ዘንድ ፡ ተቀባይነት ፡ ሊኖረው ፡ ይችላል ፤ ወይም ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ ውሉን ፡ ለማፍረስ ፡ የሚያስችሉ ፡ ምክንያቶች ፡ መኖራቸውን ፡ ላያውቅ ፡ ይችላል ። ካልፈረሰ ፡ በቀር ፡ ይህን ፡ ዓይነት ፡ ውል ፡ ጽኑ ፡ ከሆነው ፡ ውል ፡ ለመለየት ፡ ያዳግታል ።

እንግዲህ ፡ ውሉ ፡ ጽኑነቱን ፡ የሚያጣው ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ሄዶ ፡ ከተፈጸመበት ። ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ ነው ፡ ወይስ ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ እንዲፈርስ ፡ ከተደረገበት ፡ ጀምሮ ፡ ለሚቀጥሉት ፡ ጊዜያት ፡ ብቻ ፡ ነው ? አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ውልን ፡ ማፍረስ ፡ ተዋዋዮቹ ፡ ውለታ፡ ከመደረጉ ፡ በፊት ፡ እንደ ፡ ነበሩት ፡ ሁኔታ ፡ እንዲመለሱ ፡ ማድረግና ፡ ውለታውን ፡ ለመፈጸም ፡ የተሠራ ፡ ሁሉ ፡ ቀሪ ፡ ሆኖ ፡ በማናቸውም ፡ አኳኋን ፡ ውጤት ፡ የሌለው ፡ እንዲሆን ፡ የሚያደርግ ፡ ነው ።[56] ይህም ፡ ውሎች ፡ የማይጸኑት ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ሄዶ ፡ ከተፈጸሙበት ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ ስለሆነ ፡ ከመጀመሪያው ፡ እንዳልነበሩ ፡ ይቆጠራሉ ፡ ማለት ፡ ነው ። ለምሳሌ ፡ ሀ ፡ ለለ ፡ አንድ ፡ መኪና ፡ እንዲሸጥ ፡ ሁለቱም ፡ በአንድ ፡ በማይጸና ፡ ውል ፡ ይስማማሉ ። በኋላም ፡ ሀ ፡ ውሉን ፡ ቢያፈርሰው ፡ ውጤቱ ፡ መኪናውን ፡ ለሀ ፡ የመኪናውን ፡ ዋጋ ፡ ደግሞ ፡ ለለ ፡ መመለስ ፡ ነው ፡ ሀ ፡ ከመጀመሪያ ፡ ጀምሮ ፡ ለሁልጊዜ ፡ የመኪናው ፡ ባለቤት ፡ እንደነበረ ፡ ይቆጠራል።

ከዚህ ፡ ያለፈውን ፡ ሁኔታ ፡ ከመንካት ፡ ደንብ ፡ የሚለዩ ፡ ሁለት ፡ በሕግ ፡ የታወቁ ፡ ሁኔታዎች ፡ አሉ ። ውሉን ፡ ለመፈጸም ፡ የተሠራው ፡ ሥራ ፡ ውጤት ፡ ሶስተኛ ፡ ወገንን ፡ የሚጠቅም ፡ ከሆነ ፡ እንደ ፡ ረጋ ፡ እንዲቀር ፡ ይደረጋል ።[57] ለምሳሌ ፡ ለ ፡ ደግሞ ፡ መኪናውን ፡ ለሐ ፡ ሸጦ ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ ሐ ፡ መኪናውን ፡ ለሀ ፡ እንዲመልስ ፡ ማስገደድ ፡ ትክክለኛ ፡ አይሆንም ። በሀ ፡ እና ፡ በለ ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ ግንኙነት ፡ በገንዘብ ፡ ክፍያ ፡ ብቻ ፡ ይፈጸማል ። የተሠራውን ፡ ሥራ ፡ ለማፍረስ ፡ የማይቻል ፡ ሲሆን ፡ ወይም ፡ አስቸጋሪ ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ፡ ወይም ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ መሰናክል ፡ የሚያመጣ ፡ ሲሆን ፡ እነዚህ ፡ የተሠሩት ፡ ሥራዎች ፡ አይፈርሱም ።[58] ለምሳሌ ፡ መኪናው ፡ በአደጋ ፡ ቢጠፋ ፡ ለባለቤቱ ፡ ለመመለስ ፡ አይቻልም ። ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ተገቢ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ የገመተውን ፡ ገንዘብ ፡ ለ ፡ ለሀ ፡ እንዲከፍል ፡ ማዘዝ ፡ አለበት ።

---

54. "ሕጋዊ ፡ ውጤት ፡ የለውም" ፡ ስለሚሉት ፡ ቃላት ፡ ትርጉም ፡ በገጽ ፡ 90 የተደረገውን ፡ ክርክር ፡ ይመለከቷል ።

55. ምንም ፡ እንኳን ፡ የእንግሊዘኛው ፡ ቅጂ ፡ ቍ. ፰፻፲፬ ፡ "አይጸናም" ፡ ቢልም ፡ "ኑል" "nul" የሚለው ፡ የፈረንሣይኛ ፡ ቃል ፡ "ፈራሽ" ተብሎ ፡ ቢተረጐም ፡ የተሻለ ፡ ነው ። የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ውልን ለማፍረስ ፡ የሚቻለው ፡ የጽሑፍ ፡ ማስረጃ ፡ በሌለበት ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ አይደለም ። ስምምነቱ ፡ ውል ፡ ስለሆነ ፡ ስለ ፡ ውል ፡ የተደነገጉት ፡ ጠቅላላ ፡ ደንቦች ፡ ይፈጸሙበታል ። ለምሳሌም ፡ ውሉ ፡ ከተዋዋዮቹ ፡ በአንደኛው ፡ የፈቃድ ፡ ጉድለት ፡ ወይም ፡ ችሎታ ፡ ማጣት ፡ ሊፈርስ ፡ ይችላል ።

56. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍ. ፩ሺ፰፻፰ ።

57. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍ. ፩ሺ፰፻፲፮ ።

58. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍ. ፩ሺ፰፻፲፯ (፩) ።

ጉዳዩ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ያልዋለ ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ውልን ፡ የሚመለከት ፡ ከሆነ፡ ማለት ፡ የሽርክናው ፡ ማኅበር ፡ ሥራውን ፡ ያልጀመረ ፡ ከሆነ ፡ ከላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ ጠቅላላ ፡ ድንጋጌ ፡ ለመጠቀም ፡ ይቻላል ። ስለዚህም ፡ ተዋዋዮቹን ፡ ፊት ፡ ወደ ፡ ነበሩበት ፡ ሁኔታ ፡ ለመመለስ ፡ ይመቻል ። ነገር ፡ ግን ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ የሽርክናው ፡ ማኅበር ፡ ሥራውን ፡ የጀመረ ፡ ምናልባትም ፡ ለብዙ ፡ ጊዜ ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ የቆየ ፡ ይሆናል ፤ ይህንንም ፡ ሁኔታ ፡ ናቅ ፡ አድርጎ ፡ ማለፍ ፡ ያዳግታል ። በዚህም ፡ ጊዜ ፡ ከሽርክናው ፡ ማኅበር ፡ ጋራ ፡ የተዋዋሉ ፡ የሶስተኛ ፡ ወገኖች ፡ ጥቅም ፡ ችግር ፡ ሊፈጥር ፡ ይችላል ። በማኅበረተኞቹ ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ ሁኔታም ፡ የተወሳሰበ ፡ ሊሆን ፡ ስለሚችል ፡ ቀድሞ ፡ እንደ ፡ ነበሩት ፡ ሁኔታ ፡ እንዲመለሱ ፡ ለማድረግ ፡ አስቸጋሪ ፡ ምናልባትም ፡ የማይቻል ፡ ይሆናል ። እነዚህ ፡ ጉልህ ፡ የሆኑ ፡ ችግሮች ፡ ስለሚገጥሙን ፡ ውል ፡ ሲፈርስ ፡ ያለፈውን ፡ ሁኔታ ፡ የመንካት ፡ ድንጋጌ ፡ በሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ላይ ፡ ጠቅላላ ፡ ተፈጻሚነት ፡ ሳይኖረው ፡ በአንዳንድ ፡ የተለዩ ፡ ሁኔታዎች ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ተፈጻሚ ፡ እንዲሆን ፡ ይደረጋል ። ስለዚህም ፡ የሽርክናው ፡ ማኅበር ፡ ውል ፡ እስኪፈርስ ፡ ድረስ ፡ እንደጸና ፡ ተቆጥሮ ፡ ከፈረሰበት ፡ ቀጥሎ ፡ ላለው ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ የማይጸና ፡ ይሆናል ።[59]

የሽርክናው ፡ ማኅበር ፡ ውል ፡ የወደፊቱን ፡ ሁኔታ ፡ እንደሚነካ ፡ ሆኖ ፡ በፈረሰ ፡ ጊዜ ፡ መሠረት ፡ የሚሆን ፡ ውል ፡ ስለማይኖር ፡ የሽርክናው ፡ ማኅበር ፡ ራሱ ፡ ሊኖር ፡ አይችልም ። ተዋዋዮቹ ፡ በማናቸውም ፡ ውል ፡ ስለማይገደዱ ፡ የያንዳንዳቸው ፡ ጉዳይ ፡ መለየት ፡ ባንድነት ፡ የተያዘውም ፡ ገንዘብ ፡ ደግሞ ፡ መከፋፈል ፡ አለበት ። የሽርክናው ፡ ማኅበር ፡ ውል ፡ መፍረስ ፡ የሽርክናውን ፡ ማኅበር ፡ መፍረስ ፡ ሲያስከትል ፡ ይህም ፡ ራሱ ፡ የሽርክናውን ፡ ማኅበር ፡ ሒሳብ ፡ ማጣራት ፡ ያስከትላል ።

በፍርድ ፡ ቤት ፡ እንዲፈርሱ ፡ ሊደረጉ ፡ ስለሚችሉ ፡[60] የሽርክና ፡ ማኅበሮችና ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ስለቆዩ ፡[61] የሽርክና ፡ ማኅበሮች ፡ ጉዳይ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተጠቀሱት ፡ ጉልህ ፡ ችግሮች ፡ ማለት ፡ የሶስተኛ ፡ ወገኖች ፡ ጥቅም ፡ እና ፡ በማኅበርተኞቹ ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ ግንኙነት ፡ አስቸጋሪነት ፡ ስለገጠሙአቸው ፡ የፈረንሣይ ፡ የሕግ ፡ ሊቃውንት ፡ "በሕግ ፡ ሳይታወቁ ፡ የሚሠሩ" ("ዲ ፡ ፋክቶ") የሽርክና ፡ ማኅበሮች ፡ የሚል ፡ አንድ ፡ በሕረ ፡ አሳብ ፡ (ቲዎሪ) እንዲፈጥሩና ፡ እንዲያደረጁ ፡ አስገድድዋቸዋል ። በዚህም ፡ በሕረ ፡ አሳብ ፡ መሠረት ፡ የሽርክናው ፡ ማኅበር ፡ ውል ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ አማካይነት ፡ ፈርሷል ፡ እስኪባል ፡ ድረስ ፡ እንደጸና ፡ ይቆያል ። የሽርክናውን ፡ ማህበር ፡ ውል ፡ ለማስፈጸም ፡ ሳይሆን ፡ የሽርክናው ፡ ማኅበር ፡ ሒሳብ ፡ እንዲጣራ ፡ ለማድረግ ፡ ሶስተኛ ፡ ወገኖች ፡ ወይም ፡ ማኅበረተኞቹ ፡ የሽርክናው ፡ ማኅበር ፡ "በሕግ ፡ ሳይታወቅ ፡ የሚሠራ" ("ዲ ፡ ፋክቶ") ፡ መሆኑን ፡ በማናቸውም ፡ ዓይነት ፡ ማስረጃ ፡ ለማረጋገጥ ፡ ይችላሉ ።[62] በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ድንጋጌዎች ፡ በመጠቀም ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ተስማሚ ፡ ነው ፡ በማለት ፡ ይህን ፡ መፍትሄ ፡ ቀደም ፡ ብለን ፡ አቅርበናል ።

59. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቊ. ፩ሺ፰፻፲፮ (፩) ።
60. ፕሮፌሰር ፡ ዳቪድ ፡ ራሳቸው ፡ እንደ ፡ ልዩ ፡ የሚቆጠረው ፡ ደንብ ፡ ጠቅላላ ፡ ደንብ ፡ ሊሆን ፡ መቻሉን፡ ተገንዝበዋል ። በፕሮፌሰር ፡ ዳቪድ ፡ የተጻፈውን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ የመጀመሪያ ፡ ፕሮዤ ፡ (አቫን ፡ ፕሮዤ) ፡ (ያልታተመ) ፡ ይመለከቷል ።
61. በፈረንሣይ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ የሽርክና ፡ ውል ፡ በጽሕፈት ፡ ካልሆነ ፡ እንደሚፈርስ ፡ ሁሉ ፡ ሳይመዘገብ ፡ ቢቀርም ፡ እንደሚፈርስ ፡ ያስተውኋል ። የ፲፰፻፷፯ ዓ ፡ ም ፡ ሕግ ፡ ቊ. ፶፰ ፡ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቊ ፴፫ ፡ የተጠቀሰ ።
62. ኤ. ሞሮ ፡ አሶሲዮን ፡ ኤ ፡ ፓርቲሲፓስዮን ፡ ኤ ፡ ሶሲቴ ፡ ደ ፡ ፌ ፡ (፲፱፻፶፰) ፡ ገጽ ፡ ፪፻፳፫ ።

የፈረንሣይ ፡ ሕግ ፡ ለሽርክና ፡ ማኅበሮች ፡ የሚሆን ፡ የተለየ ፡ አጠቃላይ ፡ በሕረ-አሳብን ፡ ሲያደረጅ ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ውሎች ፡ ከሌሎች ፡ ውሎች ፡ ይልቅ ፡ ይበልጥ ፡ አስቸጋሪ ፡ መሆናቸውን ፡ እና ፡ እንደ ፡ ተራ ፡ ውሎች ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ፡ ብቻ ፡ የማይወሰኑ ፡ መሆናቸውን ፡ አውቆአል ። የሽርክናው ፡ ማኅበር ፡ ውል ፡ በሥራ፡ ላይ ፡ ከዋለ ፡ እና ፡ ለወደፊቱ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ የማዋሉ ፡ ጥያቄ ፡ ካላጋጠመን ፡ በቀር ፡ የዚህ ፡ አስተሳሰብ ፡ አንዱ ፡ ውጤት ፡ ያልተጻፈውን ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ውል ፡ እና ፡ ተጽፎ ፡ ያልተመዘገበውን ፡ የሽርክና ፡ ስምምነት ፡ እኩል ፡ አድርጎ ፡ መመልከት ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ በሁለቱ ፡ ውሎች ፡ መካከል ፡ ሁለት ፡ ከፍ ፡ ያሉ ፡ ልዩነቶች ፡ አሉ ።

በመጀመሪያ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ለውሉ ፡ አጻጻፍ ፡ የተደነገገው፡ ፎርም ፡ አልተጠበቀም ፡ በማለት ፡ ከተዋዋዮቹ ፡ አንዱ ፡ ወይም ፡ ማንኛውም ፡ ጥቅም ያለው ፡ ሰው ፡ ውሉ ፡ እንዲፈርስ ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ። [63] የዚህም ፡ ውጤት ፤ ጥቅም ፡ ያላቸው ፡ ሶስተኛ ፡ ወገኖች ፡ የሽርክናው ፡ ማኅበር ፡ እንዲፈርስና ፡ ሒሳብ፡ እንዲጣራ ፡ ለማስገደድ ፡ እንዲችሉ ፡ ያደርጋቸዋል ። ከማኅበሩ ፡ ላይ ፡ ገንዘብ ፡ የሚጠይቁ ፡ ሰዎች ፡ እና ፡ምናልባትም ፡ የማኅበረተኞቹ ፡ የግል ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ "ጥቅም ፡ ያላቸው" ሰዎች ፡ ናቸው ፡ ለማለት ፡ ይቻል ፡ ይሆናል ። በጽሑፍ ፡ በተደረገ ፡ ውል ፡ የተቋቋመ ፡ እና ፡ ያልተመዘገበ ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ እንዲፈርስ ፡ ለመጠየቅ ፡ የሚችሉት ፡ ማኅበርተኞቹ ፡ ብቻ ፡ ናቸው ።

ሁለተኛ ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ የሽርክናው ፡ ማኅበር ፡ ገንዘብ ፡ የሚከፋፈለው ፡ በሽርክናው ፡ ማኅበር ፡ ውል ፡ ሳይሆን ፡ በንግድ ፡ ሕጉ ፡ መሠረት ፡ ነው ። ማኅበርተኞቹ ፡ በፈቃዳቸው ፡ የትርፉን ፡ አከፋፈል ፡ በሽርክናው ፡ ማኅበር ፡ ውል ፡ ውስጥ ፡ በመጀመሪያ ፡ ሊወስኑት ፡ ይችላሉ ።[64] ይህንን ፡ የሚወስን ፡ ድንጋጌ ፡ በሽርክናው ፡ ማኅበር ፡ ውል ፡ ውስጥ ፡ ካልኖረ ፡ ግን ፡ ትርፉን ፡ እኩል ፡ ይካፈሉታል ።[65] በፈራሽ ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ውል ፡ መሠረት ፡ የሽርክናው ፡ ማኅበር ፡ ሒሳብ ፡ እንዲጣራ ፡ ማድረግ ፡ ውሉን ፡ በከፊል ፡ ለወደፊት ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ማዋል ፡ ስለሚሆን ፡ የሽርክናው ፡ ውል ፡ በሚፈርስበት ፡ ጊዜ ፡ ማኅበረተኞቹ ፡ ለመስማማት ፡ እንዳልቻሉ ፡ መቆጠር ፡ አለባቸው ። በዚህን ፡ ጊዜ ፡ ውሉ ፡ በሞላ ፡ ስለሚፈርስ ፡ በከፊል ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ለማዋል ፡ አይቻልም ። ይህም ፡ ሁለተኛው ፡ አነጋገር ፡ ዋጋ ፡ የሚኖረው ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ውል ፡ መፍረሱን ፡ ከተቀበልን ፡ መሆኑን ፡ ማስታወስ ፡ ያሻል ። ከላይ ፡ እንደተጠቀሰው ፡ ውሉ ፡ የሚፈርሰው ፡ ከመቅጽበት ፡ አይደለም ፤ የሽርክናው ፡ ማኅበር ፡ ውል ፡ የማይጸና ፡ ነው ፡ ሳይባል ፡ ለምሳሌ ፡ ማኅበረተኞቹ ፡ ማኅበሩ ፡ እንዲፈርስ ፡ ሲስማሙ ፡ ማኅበሩ ፡ ሊፈርስ ፡ ይችላል ። በዚህም ፡ ጊዜ ፡ ገንዘቡ ፡ በስምምነቱ ፡ መሠረት ፡ ይከፈላል ።[66]

<u>የሽርክና ፡ ማኅበሮችን ፡ የሚመስሉ ፡ ማኅበሮች ፡ እና ፡ ሶስተኛ ፡ ወገኖች ፡</u>

አንድ ፡ ሦስተኛ ፡ ወገን ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ መስሎት ፡ ከታየው ፡ ከአንድ ፡ ድርጅት ፡ ጋር ፡ ከተዋዋለ ፡ በኋላ ፡ አንዱን ፡ ሰው ፡ እንደ ፡ አንድ ፡ ማኅበረተኛ ፡ አላፊ ፡ ለማድረግ ፡ በሚፈልግበት ፡ ጊዜ ፡ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ የተዛመደ ፡ ችግር ፡

---

63. ሬፔር ፡ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍ. ፩ ፡ የተጠቀሰ ፡ ገጽ ፡ ፪፻፺፪ ።
64. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍ. ፩ሺ፳፻፳ ፡ (፪) ።
65. የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቍ. ፪፻፹ ፡ (፫) ።
66. ከዚያው ፡

ይገጥመናል ። ይኸ ፡ ሦስተኛ ፡ ወገን ፡ ይኸንን ፡ ሰው ፡ አላፊ ፡ ለማድረግ ፡ ሲፈልግ ፡ ማስረዳት ፡ ያለበት ፡ ሰውዬው ፡ በይፋ ፡ ለሕዝብ ፡ እንደ ፡ ማኅበረተኛ ፡ መስሎ ፡ ራሱን ፡ ማቅረቡን ፡ ማለት ፡ በግልጽ ፡ የተነገረ ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ የነበረ ፡ ማስመሰሉን ፡ ነው ፡ ወይስ ፡ የሽርክናውን ፡ ማኅበር ፡ ውል ፡ አቋሞች ፡ ማለት ፡ በጉዳዩ ፡ ውስጥ ፡ ያሉት ፡ ሰዎች ፡ ማኅበረተኞች ፡ ለመሆን ፡ ፈቃድ ፡ እንደነበራቸው ፡ ነው ? ምንም ፡ እንኳን ፡ ይኸንን ፡ ጥያቄ ፡ የሚመልስልን የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ባይኖርም ፡ በሌሎች ፡ አገሮች ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ የዋሉትን ፡ ደንቦች፡ በመመልከት ፡ ተስማሚ ፡ ሊሆኑ ፡ የሚችሉ ፡ መፍትሔዎችን ፡ ለማቅረብ ፡ ይቻላል።

ይኸንን ፡ ችግር ፡ ለማስወገድ ፡ በጣም ፡ የገፋበት ፡ የአሜሪካን ፡ ሕግ ፡ ነው ። የተቋቋመው ፡ ድርጅት ፡ እውነተኛ ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ በማይሆንበት ፡ ጊዜ ፡ ማኅበሩ ፡ ያለ ፡ መስሎአቸው ፡ በቅን ፡ ልቡና ፡ የሚዋዋሉትን ፡ የሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ ጥቅም ፡ ለመጠበቅ ፡ ሲባል ፡ የዚህን ፡ ዓይነት ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ የሚያጠቃልል ፡ አንድ ፡ መሠረተ፡አሳብ ፡ ደረጀ ። በዚህም ፡ አሳብ ፡ መሠረት ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ "በአንድ ፡ መኖሩ ፡ በታወቀ ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ውስጥ ፡ ወይም ፡ ከአንድ ፡ ወይም ፡ ከአንድ ፡ በላይ ፡ ከሆኑት ፡ ሌሎች ፡ ሰዎች ፡ ጋራ ፡ ማኅበረተኛ ፡ የሆነ ፡ በማስመሰል ፡ ራሱን ፡ በራሱ ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ ሰው ፡ አማካይነት ፡ ለሕዝብ ፡ ከአስታወቀ፡" እንደ ፡ አንድ ፡ ማኅበረተኛ ፡ በሙሉ ፡ አላፊነት ፡ ተጠያቂ ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ።[67]

በኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ እውነተኛ ፡ ማኅበረተኛም ፡ ባይሆን ፡ አውቆ ፡ ስሙ ፡ በማኅበሩ ፡ ስም ፡ ውስጥ ፡ ሲጻፍ ፡ ዝም ፡ ያለ ፡ እንደሆነ ፡ እንደ ፡ ሌሎቹ ፡ ማኅበረተኞች ፡ ለማኅበሩ ፡ ግዴታዎች ፡ ሁሉ ፡ ተጠያቂ ፡ ይሆናል ።[68] ምንም ፡ እንኳን ፡ በማስመሰል ፡ የተፈጠረ ፡ የሽርክና ፡ ማኅበርን ፡ የሚይዝ ፡ አጠቃላይ ፡ ደንብ፡ ባይኖር ፡ በአንድ ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ማኅበረተኛ ፡ ባይሆንም ፡ ሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ ማኅበረተኛነቱን ፡ እንዲያምኑ ፡ ከተደረጉ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተጠቀሰው ፡ ድንጋጌ ፡ እነዚህን ፡ ሶስተኛ ፡ ወገኖች ፡ እንደሚጠብቅ ፡ ለመረዳት ፡ ይቻላል ። ይህም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ በአሜሪካን ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ የሚመስል ፡ አንድ ፡ መሠረተ ፡ አሳብ ፡ እንዲፈጥሩ ፡ ያደርጋቸው ፡ ይሆናል ።

ምንም ፡ እንኳን ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ የአሜሪካኑን ፡ መፍትሔ ፡ ባይከተሉም ፡ በሚገጥማቸው ፡ በያንዳንድ ፡ ጉዳይ ፡ የሚያመጡት ፡ ውጤት ፡ ከዚህ ፡ መፍትሔ ፡ በጣም ፡ የተለየ ፡ አይሆንም ። በማስመሰል ፡ የተፈጠረ ፡ የሽርክና ፡ ማኅበርን ፡ የሚያጠቃልለውን ፡ የአሜሪካን ፡ መሠረተ ፡ አሳብ ፡ የፈረንሳይ ፡ ሕግ ፡ ስለማይቀበለው ፡ የአሜሪካኑ ፡ መፍትሔ ፡ ተቃራኒ ፡ የሆነውን ፡ አሳብ ፡ በአንድ ፡ የፈረንሣይ ፡ የፍርድ ፡

67 . ውሉ ፡ ይፍረስ ፡ ወይም ፡ አይፍረስ ፡ የሚል ፡ ክርክር ፡ ይነሳ ፡ ይሆናል ። ክርክሩንም ፡ የሚከተሉትን ፡ ሁለት ፡ መሠረተ ፡ አሳቦች ፡ በመከተል ፡ ለማስወገድ ፡ ይቻላል ። ክርክሩ ፡ በማኅበርተኞቹና ፡ በሌላ ፡ ሶስተኛ ፡ ወገን ፡ መካከል ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ ሶስተኛው ፡ ወገን ፡ ቅድሚያ ፡ ያገኛል ። የውሉ ፡ መፍረስ ፡ አላፊነት ፡ የሚመለከተው ፡ ማኅበርተኞቹን ፡ ስለሆነ ፡ በሌላ ፡ ሶስተኛ ፡ ወገን ፡ ላይ ፡ እንዲጠቀሙበት ፡ ሊፈቀድላቸውም ፡ አይገባም ። ክርክሩ ፡ በሶስተኛ ፡ ወገኖች ፡ ወይም ፡ በማኅበረተኞች ፡ መካከል ፡ ከሆነ ፡ መፍረሱን ፡ የሚሹት ፡ ማኅበርተኞች ፡ ቅድሚያ ፡ ያገኛሉ ።

ማኅበርተኞቹ ፡ የሽርክና ፡ ውላቸው ፡ እንዲፈርስ ፡ በሚፈልጉበትና ፡ ሶስተኛ ፡ ወገኖች ፡ ደግሞ ፡ እንዳይፈርስ ፡ በሚፈልጉበት ፡ ጊዜ ፡ የነዚህ ፡ መሠረተ ፡ አሳቦች ፡ ውጤት ፡ ምን ፡ ይሆናል ? ሶስተኛውን ፡ ወገን ፡ የሚመለከቱ ፡ ክርክሮች ፡ በሙሉ ፡ እስከተፈጸሙበት ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ የሽርክናው ፡ ማኅበር ፡ ውል ፡ ጽኑ ፡ ሆኖ ፡ ይቆያል ። ክርክሩ ፡ እንዳለቀ ፡ ማኅበርተኞቹ ፡ ወይም ፡ ከማኅበርተኞቹ ፡ አንዱ፡ ውሉ ፡ እንዲፈርስ ፡ ክስ ፡ ለማቅረብ ፡ ይችላል ። እንግዲህ ፡ ማንኛውም ፡ ማኅበርተኛ፡ የውሉን ፡ መፍረስ ፡ ከሶስተኛው ፡ ወገን ፡ ለሚሰነዘር ፡ ክርክር ፡ እንደ ፡ መከላከያ ፡ ለማቅረብ ፡ አይችልም ።

68 . ዩኒፎርም ፡ ፓርትነርሺፕ ፡ አክት ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍ. ፴፩ የተጠቀሰ ፡ ቍ. ፲፯ ።

ጉዳይ ፣[69] ውስጥ ፣ ልናገኘው ፣ እንችላለን ። በዚህም ፣ ጉዳይ ፣ አንድ ፣ ባንክን ፣ ለማ ካሄድ ፣ የተቋቋመ ፣ እና ፣ "በሕግ ፣ ሳይታወቅ ፣ የሚሠራ ፣ " አንድ ፣ የሽርክና ፣ ማኅ በር ' በሕጉ ፣ ባይታወቅም ፣ በአባትና ፣ በልጁ ፣ መካከል ፣ መኖሩ ፣ የተረጋገጠ ፤ ነው ፣ ተብሎ ፣ ተወስኖአል ። ከቀረቡትም ፣ ማስረጃዎች ፣ መካከል ፣ ልጁ ፣ የባንክ ፣ ባለሙያ ፣ ነኝ ፣ እያለ ፣ ደጋግሞ ፣ መናገሩን ፣ የባንኩ ፣ ስም ፣ "ቻርልስ ፣ ዶሪያንትና ፣ ኩባንያው ፣ የባንክ ፣ ሰዎች"(የሽርክና ፣ ማኅበር ፣ መሆኑን ፣ የሚገልጽ) መሆኑን ፣ ልጁም ፣ በእንደ ራሴነት ፣ ሥልጣን ፣ መፈረሙን ፣ ሳያሳይ ፣ በባንኩ ፣ ስም ፣ መፈረሙን ፣ የሚያረጋ ግጡ ፣ ነበሩ ፤ ፍርድ ፣ ቤቱ ፣ ፍሬ ፣ ነገር ፣ አድርጎ ፣ የቆጠረው ፣ በሁለቱ ፣ መካከል ፣ ያለውን ፣ ውስጣዊ ፣ ግንኙነት ፣ ሳይሆን ፣ ለሕዝቡ ፣ ምን ፣ መስለው ፣ መታየታቸውን ፣ ነው ።ይህም ፣ ውጤት ፣ በጠቅላላው ፣ የውል ፣ ሕግ ፣ የተደገፈ ፣ ነው ። ምክንያቱም፣ በዚህ ፣ ሕግ ፣ መሠረት ፣ አንድ ፣ ሰው ፣ የተገለጸውን ፣ ፈቃድ ፣ ተቀብሎ ፣ ያልተገለጹ ትን ፣ የማገድ ፣ ቃላት ፣ ላይቀበል ፣ ስለሚችል ፣ ነው ። በአንድ ፣ በኩል ፣ ውጤቱ ፣ ያስገርማል ፤ ምክንያቱም ፣ ፍርድ ፣ ቤቱ ፣ ሶስተኛ ፣ ወገኖች ፣ በጉዳዩ ፣ ካሉበት ፣ የሽር ክና ፣ ማኅበር ፣ አለ ፣ ሲል ፣ ጉዳዩ ፣ በ "ማኅበርተኞች" መካከል ፣ ሲሆን ፣ ግን ፣ የሽር ክና ፣ ማኅበር ፣ የለም ፣ ሊል ፣ በመቻሉ ፣ ነው ። "ማኅበርተኞቹ" ራሳቸው ፣ በውስ ጣዊው ፣ ግንኙነታቸው ፣ እንደ ፣ አንድ ፣ የሽርክና ፣ ማኅበር ፣ መሥራታቸውን ፣ ማሳ የት ፣ አለባቸው ።

በዚህ ፣ በፈረንሣይ ፣ ሕግ ፣ አስተሳሰብ ፣ መሠረት ፣ የሚመጣው ፣ ውጤት ፣ በአ ሜሪካን ፣ ሕግ ፣ መሠረት ፣ ከተገኘው ፣ ውጤት ፣ ጋራ ፣ በጣም ፣ ተመሳሳይ ፣ ነው ። የአሜሪካኑ ፣ ደንብ ፣ የሶስተኛ ፣ ወገኖችን ፣ ጥቅም ፣ በመጠበቅ ፣ በኩል ፣ ከእውነተ ኛው ፣ ሁኔታ ፣ ጋራ ፣ የተቀራረበ ፣ በመሆኑ ፣ ብልጫ ፣ አለው ። ጉዳዩ ፣ በማኅበርተ ኞች ፣ መካከል ፣ ካልሆነ ፣ በቀር ፣ የወገኖቹ ፣ ውስጣዊ ፣ ፈቃድ ፣ ምንም ፣ አግባብ ፣ የለ ውም ። የፈረንሣዮችን ፣ አስተሳሰብ ፣ ከተከተልን ፣ ሶስተኛው ፣ ወገን ፣ የተጻፈ ፣ የሽ ርክና ፣ ማኅበር ፣ ውል ፣ ለማቅረብ ፣ አለመቻሉን ፣ አስቀድመን ፣ ስለተቀበልን ፣ የሚ ፈርስ ፣ የሽርክና ፣ ማኅበር ፣ መኖሩን ፣ አሳየ ፣ ማለት ፣ ነው ። ይህም ፣ ከዚህ ፣ በላይ ፣ እንደተገለጸው ፣ ሁሉ ፣ ላለፈው ፣ ጊዜ ፣ እንደጸና ፣ ተቆጥሮ ፣ ለወደፊት ፣ ብቻ ፣ ጽኑ ነት ፣ እንደሌለው ፣ ሆኖ ፣ ይቆጠራል ።

## መደምደሚያ ።

ፍርድ ፣ ቤቶች ፣ አንድ ፣ የንግድ ፣ መደብር ፣ በሁለት ፣ ወይም ፣ ከሁለት ፣ በሚበ ልጡ ፣ ሰዎች ፣ አማካይነት ፣ እንዲሠራ ፣ የሚያደርግ ፣ ስምምነት ፣ በገጠማቸው ፣ ጊዜ ፣ ውሉ ፣ በንግድ ፣ ሕግ ፣ መሠረት ፣ የተደረገ ፣ "የሽርክና ፣ ማኅበር ፣ ውል" መሆ ኑን ፣ መጀመሪያ ፣ መወሰን ፣ አለባቸው ። እነዚህ ፣ ሁኔታዎች ፣ ተሟልተው ፣ከተገኙ፣ ተዋዋዮቹ ፣ የንግድ ፣ ሕግ ፣ መኖሩን ፣ ባያውቁም ፣ ልማዳዊ ፣ ደንቦችንና ፣ ፎርሞችን ፣ ከተከተሉ ፣ በጽሑፍ ፣ እንዲሆን ፣ ወይም ፣ በማስታወቂያ ፣ እንዲገለጽ ፣ የሚሉት ፣ ድንጋጌዎች ፣ ባይፈጸሙም ፣ ውሉ ፣ እንደ ፣ አንድ ፣ የሽርክና ፣ ማኅበር ፣ ውል ፣ መቆ ጠር ፣ አለበት ። ፎርሞችን ፣ የሚመለከቱትን ፣ ድንጋጌዎች ፣ አለመከተል ፣ "ልማዳ ዊ ፣ የሽርክና ፣ ማኅበሮችን" ብቻ ፣ የማይመለከቱ ፣ ልዩ ፣ ችግሮችን ፣ ይፈጥራል ። ሰዎች ፣ የንግድ ፣ ሕግን ፣ ለመከተል ፣ አስበው ፣ አንዳንድ ፣ የፎርም ፣ ግዴጆችን ፣ ሳይ

69 የንግድ ፣ ሕግ ፣ ቍ. ፪፻፹፩ (፫) ።

70. ዶርዬ፣ ሲ፣ ኮውቢ ፣ ኤ፣ ኳሊቴ፣ (ቦርዶ ፣ ፍራንስ ፣ ጁላይ ፣ ፳ ፣ ፲፱፻፴፱)፣ ሬቡ፣ ደ፣ ሶሲቴ ፣ ፲፱፻፴፱ ፣ ገጽ፣ ፪፻፳ ።

ፈጽሙ ፡ በሚቀሩበት ፡ ጊዜ ፡ እነዚሁ ፡ ችግሮች ፡ ተመልሰው ፡ ይመጣሉ ። እነዚህን ፡ ማኅበሮች ፡ በእውነቱ ፡ እንዳሉ ፡ ("ዲ ፡ ፋክቶ") አድርጐ ፡ መቍጠር ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተጠቀሱትን ፡ ችግሮች ፡ ያስወግድ ፡ ይሆናል ፡ የሚል ፡ አሳብ ፡ ቀርቧል ።

ሁለት ፡ "በሕግ ፡ ሳይታወቁ ፡ የሚሠሩ" ("ዲ ፡ ፋክቶ") የሽርክና ፡ ማኅበሮችን ማለት ፡ ያልተመዘገበ ፡ የሽርክና ፡ ማኅበርንና ፡ ባልተጻፈ ፡ ውል ፡ የተፈጠረ ፡ የሽርክና ፡ ማኅበርን ፡ ተመልክተናል ። በሁለቱም ፡ በኩል ፡ የተመለከትነው ፡ በንግድ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኘው ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ትርጓሜ ፡ ከተሟላ ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ የተጻፈ ፡ ውል ፡ ባይኖር፡ወይም፡በማስታወቂያ ፡ ባይገለጽ ፡ ማኅበሮቹን ፡ እንደ ፡ የሽርክና፡ ማኅበሮች ፡ ከመቁጠር ፡ የሚያግድ ፡ ነገር ፡ አለመኖሩን ፡ ነው ። በተጨማሪም ፡ በሁለቱም ፡ በኩል ፡ ማኅበረተኞቹ ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ በመካከላቸው ፡ ብቻ ፡ ወይም ፡ ከሶስተኛ ፡ ወገኖች ፡ ጋራ ፡ የፈጸሟቸው ፡ ድርጊቶች ፡ በሕግ ፡ ታውቀው ፡ የጸኑ ፡ መሆን ፡ አለባቸው ፤ ሆኖም ፡ ሁለቱም ፡ "በሕግ ፡ ሳይታወቁ ፡ የሚሠሩ" ፡ ("ዲ ፡ ፋክቶ") ማኅበሮች ፡ በሕግ ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ አይኖራቸውም ። "ዲ ፡ ፋክቶ" የሚለው ፡ ቃል ፡ ዋና ፡ ትርጉሙ ፡ ይህ ፡ ነው ።

ነገር ፡ ግን ፡ በሁለቱ ፡ መካከል ፡ አንዳንድ ፡ ልዩነቶች ፡ አሉ ። "በሕግ ፡ ሳይታወቅ ፡ የሚሠራው" ፡ ("ዲ ፡ ፋክቶ") ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ በጽሑፍ ፡ በተደረገ ፡ ውል ፡ የተደገፈ ፡ ካልሆነ ፡ መኖሩ ፡ በሕግ ፡ የሚታወቀው ፡ ላለፈው ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ነው ። ውሉ ፡ ራሱ ፡ የማይጸና ፡ ስለሚሆን ፡ ለወደፊት ፡ በሕግ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ እንዲውል ፡ አይደረግም ። የሽርክናው ፡ ማኅበር ፡ ውል ፡ ተጽፎ ፡ ሳይመዘገብ ፡ ሲቀር ፡ ውሉ ፡ ራሱ ፡ የሚጸና ፡ ስለሚሆን ፡ ለወደፊቱ ፡ ተፈጻሚነት ፡ እንዲኖረው ፡ ለማድረግ ይቻላል ። ማንኛውም ፡ ማኅበረተኛ ፡ ከፈለገ ፡ ማኅበሩን ፡ በማስመዝገብ ፡ ብቻ ፡ "በሕግ ፡ የታወቀ" ፡ ማኅበር ፡ ሊያደርገው ፡ ይችላል ። ከዚህ ፡ ልዩነት ፡ የሚመጡ ፡ ሁለት ፡ ጉልህ ፡ ውጤቶች ፡ አሉ ። አንደኛ ፡ የሽርክናው ፡ ማኅበር ፡ ያልተመዘገበ ፡ ከሆነ ፡ በማኅበረተኞቹ ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ ግንኙነት ፡ ሶስተኛ ፡ ወገኖችን ፡ የሚመለከት ፡ ቢሆንም ፡ በጽኑ ፡ ውላቸው ፡ ቁጥጥር ፡ ሥር ፡ ይሆናል ። የሽርክናው ፡ ማኅበር ፡ ውል ፡ በጽሑፍ ፡ የአልተደረገ ፡ ከሆነ ፡ ግን ፡ በማኅበረተኞቹ ፡ መካከል ፡ ያለው ግንኙነት ፡ በንግድ ፡ ሕግ ፡ ቁጥጥር ፡ ስር ፡ ይሆናል ። ሁለተኛ ፡ የተጻፈ ፡ ውል ፡ ያለው ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ እንዲፈርስ ፡ ሊያስገድዱ ፡ የሚችሉት ፡ ማኅበርተኞቹ ፡ ብቻ ፡ ሲሆኑ ፡ ያልተጻፈውን ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ውል ፡ አልተጻፈም ፡ ብሎ ፡ ሊቃወምና ፡ ማኅበሩ ፡ እንዲፈርስ ፡ ለማድረግ ፡ የሚችለው ፡ ማንኛውም ፡ "ጥቅም ፡ ያለው" ሶስተኛ ፡ ወገን ፡ ነው ።